
# ትንሣኤ



አዲስ አበባ ከተማ ግቢ ኪዳነምሀረት ቤተክርስቲያን



በጋሞ ጎፋ ሀ/ስብከት በጋሞ አውራጃ በጨንቻ ወረዳ የምትገኘው የብርብር ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ጥርና የካቲት ወር ፲፱፻፹፬ ዓ·ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በቲማባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ “ትንሣኤ” ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

## ማውጫ

### አርእስት

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ሰውን እፈልጋለሁ (ርዕስ አንቀጽ) | ፫ |
| ጥምቀተ ክርስትና | ፬ |
| ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሰሜን ወሎ ሀ/ስብከት ያደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ ከቁጥር ፩፺፺፩ የቀጠለ | ፯ |
| የመጀመሪያ ተአምር በሠርግ ቤት | ፱ |
| የጊዜ ትግል ከብፁዕ አቡነ አብርሃም | ፲ |
| ለሕብረተሰቡ እውነተኛ ፍቅር ያስፈልገዋል | ፲፪ |
| ዜና አበው | ፲፬ |
| የግሸን ማርያም ታሪክ በአጭሩ | ፲፭ |
| እንግዶችን ለመቀበል ትጉ | ፲፯ |
| ዜና ሊቃውንት | ፲፰ |
| የሴቶች ዓምድ | ፲፱ |
| ጤናችን | ፳፩ |
| የአቶ አማረ ገዛኸኝ አጭር የሕይወት ታሪክ | ፳፪ |
| ሰበካ ጉባኤና ርምጃው የመካነ ሥላሴ መሠረተ ልማት | ፳፬ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

መንፈሳዊ ሰላምታየን በማስቀደም ለማቀርባቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ እንደምትሰጡኝ እተማመናለሁ ።

፩ኛ· አለቃ ተቀባ ወርቅ እሸቴ በጻፉት ፍሬ ሃይማኖት በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ ፳፰ ላይ የገና ጾም በ፫ቱ ወንጌላውያን ኅዳር ፲፭ ቀን ተጀምሮ ፋሲካው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ሲሆን በዘመነ ዮሐንስ ግን መጀመሪያው ኅዳር ፲፬ ቀን ይሆንና ፋሲካው ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ነው ይላል ።

በዘንድሮው ዓመት ማለት በ፲፱፻፹፬ ዓ ም የገና ጾም የሚጀመረው ኅዳር ፲፭ ቀን ነው ተብሎ ተጀምሯል ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ላይ ጾሙ ኅዳር ፲፬ ቀን ተጀምሮ ፋሲካው ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ነው የሚለው ስሕተት ነው? ስሕተትስ ከሆነ እንዲስተካከል እርማት ተደርጓል ወይ? በ፬ቱም ዘመናት በስንት ተጀምሮ በስንት እንደሚፈስክ ብትገልጹልኝ?

፪ኛ· በዚሁ መጽሐፍ በገጽ ፴፩ ደግሞ ዓርብና ረቡዕ ሁለት ገሐድ ነነዌ ዓቢይ ጾም ጾመ ፍልሰታ ዓሣ አይበላባቸውም ባልና ሚስት በምንጣፍ አይገናኙባቸውም በማለት ሊቃውንት ያስተምራሉ ይላል በጾመ ነቢያትና በጾመ ሐዋርያት ዓሣ መብላትስ ሆነ ባልና ሚስት በምንጣፍ ሊገናኙባቸው የተፈቀደ ሆኖ ነው ያልተገለጸው? ወይንስ ሌላ ምክንያት አለው? ተፈቅዶስ ከሆነ ጾም መሆኑ አልተዘነጋም ወይ? እባካችሁ አብራሩልኝ?

፫ኛ· አንዳንድ የሃይማኖት መምህራን ትምህርት በሚሰጡበት ጊዜ ድንግልናቸውን ያፈረሱ ሰዎች ንስሐ ከገቡ ድንግልናቸው ይመለሳል ይላሉ እንደዚህ ከሆነ ዲቁና ያለው ሰው ድንግልናውን ካፈረሰ በኋላ ንስሐ ቢገባ ተመልሶ ዲቁና እንዳለው ሆኖ ማገልገል ይችላል ወይ? ሌላው ደግሞ ምንም ሥልጣን ሳይኖረው ድንግልናውን አፍርሶ ንስሐ ከገባ በኋላ የዲቁና መዓርግ ሊሰጠው ይችላልን? በተጨማሪ ሴትም ሆነች ወንድ ድንግልናቸውን አፍርሰው ንስሐ ቢገቡ በተክሊል ማግባት ይችላሉ ወይ?

፬ኛ· ዓሣ በዓቢይ ጾም እንደ ጾም ምግብ ተቆጥሮ አብዛኛው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነኝ የሚል ሁሉ ሲበላው ይታያል ለዚህ መፍትሔው ዓሣ በጾም አይበላም የሚለው ቃል በየሳምንቱ እሁድ እንደተአምረ ማርያም ለሕዝቡ መነገር የሚገባ ስለመሰለኝ ይህ ቢደረግ ችግሩ ምንድን ነው?

ተማሪ ፍሥሐ ሞላ
ወሎ ሀገረ ስብከት ደሴ ከተማ

<u>መልስ</u> ተማሪ ፍሥሐ ሞላ ስለ አቀረብክልን ሰላምታ እኛም በበኩላችን ሰላምታችን በማቅረብ ለጥያቄዎችህ መልስ እንሰጣለን አለቃ ተቀባ ወርቅ እሸቴ ያሳተሙት የመጽሐፍ ቃልና እኛ የምንፈጽመው ተግባር የተለየ መሆኑን ገልጸህ መጽሐፉ ነው የተሳሳተው? ወይስ እኛ ነን መጽሐፉ ከተሳሳተስ ለምን አይታረምም ስላልከው ፤ የአለቃ ተቀባ ወርቅ መጽሐፍ አልተሳሳተም ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ የተባለው የአቡሻክር መጽሐፍ በዘመነ ዮሐንስ የስብከት ጾም ኅዳር ፲፬ ቀን ተጀምሮ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን እንዲፈስክ ያዝዛል ይህንን መጽሐፍ መሠረት በማድረግ አለቃ ተቀባ ስለጻፉት አልተሳሳተም አንዳንድ ሊቃውንትም የጊዮርጊስ ወልደ አሚድን ቃል መሠረት በማድረግ ከአለቃ ተቀባ መጽሐፍ ጋር ይተባበራሉ አንተም የአለቃ ተቀባን መጽሐፍ ተከትለህ ብትጾም አትጐዳም አድልዉ ለጾም ነውና በሦስቱ ዘመናት ግን ሁልጊዜም የሚጀመረው ኅዳር ፲፭ ሲሆን የሚፈስከውም ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው ።

በሁለተኛው ጥያቄህ ላይ መጽሐፉ ዓርብና ረቡዕ ነነዌ ሁለቱ ገሃድ ዓቢይ ጾም ፍልሰታ ዓሣ አይበላባቸውም ባልና ሚስት በምንጣፍ አይገናኙባቸውም ሲል ጾመ ነቢያትንና ጾመ ሐዋርያትን ያልጠቀሳቸው በእነርሱ ዓሣ ይበላል ባልና ሚስት በምንጣፍ ይገናኙባቸዋል ። ማለቱ ነውን ስላልከው በሁሉም ሊፈጸም የማይገባ መሆኑን መጠቆሙ ነው እንጂ የጾም ታላቅና ትንሽ አለማለቱ አይደለም ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ በማንኛውም ጾም ሊፈጸሙ የማይገባቸው ተግባሮች መሆናቸውን ተገንዝበህ በጾም ወቅት ከማንኛውም ከላይ ከተጠቀሱት ነገሮች እንድትጠበቅ እና ሳስብሃለን ።

በሦስተኛው ጥያቄህ ያፈረሱ ሰዎች ንስሐ ሲገቡ እንደገና ይደነግላሉ ሲባል ዲያቆኑ ዲቁናውን አፍርሶ ንስሐ ገብቶ ይቀድሳል ማለት አይደለም እግዚአብሔር አምላክ በደሉን ይደመስስለታል ለመንግሥተ ሰማያት ያበቃዋል ማለት ነው እንጅ ያፈረሰ ሰው በተክሊል ለማግባት ይችላልን? ስላልከው ተክሊል ከሰባቱ ምሥ

(ወደ ገጽ ፰ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ሰው እፈልጋለሁ

ዲዮጋን የሚባል አንድ ሰው ሻማውን እያበራ በጠራራው ፀሐይ ገበያ ለገበያ ይዞር ነበር ሰዎች ወደ እርሱ ቀረብ ብለው ምነው? በቀትሩ የፀሐይ ብርሃን እያለልህ ሻማ አብርተህ ገበያ ለገበያ ትዞራለህ፣ ብለው ቢጠይቁት ሰው እፈልጋለሁ አላቸው ምነው ይህ በገበያው የሞላው ሰው አይደለምን ከዚህ የተለየ ምን ሌላ ሰው አለ? ቢሉት ዲዮጋን መልሶ ይህ በገበያው ተሰብስቦ የሚታየው ሰው ሁሉ መልኩና ቅርጹ ሰው መስሎ ይታያል እንጂ ሰውነቱ ሁሉ በክፋት በምቀኝነት በተንኮል በውሸት በክህደት የተበከለ ሰው መሳይ ፍጡር ነው እንጂ እውነተኛ ሰው አይደለም ፣ እኔ የምፈልገው የማይዋሽ የማይሠርቅ ተንኮል ምቀኝነት የሌለበት ሰው ነው አለ ይባላል ።

ለሁንም ለሀገር ለወገን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ታማኝ ዜጋ የሆነ የማይዋሽ የማይሰርቅ እውነትን በሐሰት የማይለውጥ ሰው ይፈለጋል ፣ እግዚአብሔር አምላክ ከሰማየ ሰማያት ውረድ ተወለድ ብሎ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጁን ወደዚህ ዓለም የላከው የጠፋውን አዳምን ለመፈለግ ነው። ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርዓያና ምሳሌ ሲሆን በምሳሌው ተፈጥሮ በግብሩ ከፈጣሪው የተለየ እንዲሆን አልታዘዘም በሥራም ፈጣሪውን እንዲመስል ታዝዟል ከኃጢአት በስተቀር ክርስቶስ እኛን መስሎ በዚህ ዓለም በለቢሰ ሥጋ ተመላልሷል እኛ እንደምንራብ ተርቧል እኛ አንደምንጠማም ተጠምቷል እኛን ከመውደዱ የተነሣ ስለ እኛ ኃጢአትና በደል ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሏል ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ይህንን ሲገልጽ "በእውነተ ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንም ተሸክሟል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔር እንደተቀሠፈ እንደተቸገረም ቈጠርነው ፣ እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን እኛ ሁላችን እንደበጎች ተቅበዘበዝን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" ብሏል ኢሳ· ፶፫·፬·

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ ልዩ መከራን የተቀበለው በግድ ሳይሆን እኛን ለማዳን ሲል በፈቃዱ ነው ክርስቶስ እኛን ለመፈለግና ለማዳን ወደ ዓለም መጥቷል እኛ እርሱን መቀበል ያለብን እንዴት አድርገን ነው? ማንም ሰው ወደማይወደው ሰው ቤት ለመሄድ አይፈልግም ወደሚወደው ሰው ግን ይሄዳል በደስታም ሆነ በመከራ አይለይም በመከራው ጊዜ ያዝናል በደስታውም ጊዜ አብሮ ይደሰታል ።

እግዚአብሔር አምላክም እኛን ስለወደደን በመከራችንም በደስታችንም አልተለየንም አይለየንም በመከራ እንደማይለየን ሲያጠይቅ የእኛን መከራ ሁሉ ተቀብሏል በደስታም ጊዜ እንደማይለየን ሲያስረዳ ከእናቱ ቅድስተ ድንግል ማርያም ጋር ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ በሰርግ ቤት ተገኝቷል በዚያ የተገኘውም የመብልና የመጠጥ የዘፈንና የጨዋታ ፍላጐት ኑሮት አይደለም አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ጸንቶ ይኑር ባለው መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ የተባረከና የተቀደሰ መሆኑን ለማስረዳት ነው በሠርግ ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሙሽራው የሚያጠጣው ጠጅ አልቆበት በአፍረት ላይ በወደቀ ጊዜ ውኃውን ወደ ጠጅ በመለወጥ የሙሽራውን ችግር አስወግዶለታል ።

በዚህ አንጻር ወደ ሰርግ ለግብዣ የሚጠሩ ወገኖች ሁሉ ለተጋቢዎች አንዳንድ ርዳታ የማድረግ መንፈሳዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ሊያውቁትና ሊረዱት ይገባል ፣ አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ማግባት መጋባት መደሰት ከክርስቶስ ዘንድ የተፈቀደ እንጂ የተከለከለ አይደለም ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ "ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ እንዳለው ከወገን ጋር መገናኘት በደስታ ጊዜ ብቻ አይደለም በኀዘንም ወቅት ብቻ መሆን የለበትም በማንኛውም ጊዜ እየተገናኙ መወያየት መመካከርና መነጋገር ያስፈልጋል" ከሌላው ያላገኘኸው ከአንተ ብቻ ያገኘኸው ምን አለህ? ለሌላው ከተሰጠ ለአንተ ያልተሠጠ ምን አለ፣ ሲል ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ሐዋርያ ተናግሯል ።

ሰው አዋቂ የሚባለው ትምህርት ቤት ገብቶ ባጠናው ጥናት ብቻ አይደለም ከዘመኑ ከአካባቢው ከችግሩም ብዙ ትምህርትን ለመገብየት የሚችል መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች ጀምሮ እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ የደረሰባት ችግር በቁጥር የሚወሰን አይደለም ብዙ ችግር ደርሶባታል ፣ ይሁን እንጂ በችግሩ የተሸነፈችበት ጊዜ አይገኝም በተለይ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ የሚደርስበት ፈተና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመሄድ ላይ ነው ቤተ ክርስቲያናችን በየዘመኑ የሚደርስባትን ፈተና ድል አድርጋ በአሸናፊነት ለመውጣት እንድትችል በእውነት የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሆኑ ወገኖች ያስፈልጋታል በአፍ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ነኝ ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም ቁም ነገሩ ሆኖ ከመገኘቱ ላይ ነው ።



ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የወሎ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ መንፈሳዊ መልእክት ሲያስተላልፉ ቤተ ክርስቲያንችን በ፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጉዳትና በ፲፯ኛው መቶ ዓመት በግራኝ ከባድ ፈተና ደርሶበታል፣ ይሁን እንጂ የደረሰባትን ፈተና ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ድል አድርጋለች የአሁኑ ፈተናዋ ግን ካለፈው ፈተና በጣም የከፋ ነው ካሉ በኋላ አሁን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተደቀነውን ፈተና ለማሸነፍ እውነተኞች ሰዎችን ትፈልጋለች በማለት ተናግረዋል ።

ብፁዕነታቸው እንደተናገሩት በዕርግጥ በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በየአቅጣጫው ተሰልፈው በእውነት የሚሠሩ ሠራተኞችን ትፈልጋለች በሀገራችን ፳ ሺህ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ካህናቱም ከ፬፻፹፭ ሺህ በላይ እንደሚሆኑ ይታመናል ። ከእነዚህ መካከል በብቃትና በጥራት ሲታዩ ሁሉም የሚያመሰግኑ ሁነው አልተገኙም ከዚህም የተነሣ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚሰነዘሩት ነቀፌታዎች ካህናቱ ብዛት እንጂ ጥራት የላቸውም እነርሱ አስተማሪዎች ሲሆኑ እርስ በእርሳቸው አይፋቀሩም ወዘተ ናቸው...

እንኳን መምህራን ለማንያኑም ቢሆኑ እርስ በእርሳቸው መነቃቀፍ መለያየት መጣላት አይገባቸውም ቤተ ክርስቲያናችንን ያለነው ርና ነቀፌታ ለማገልገል መጀመሪያ ራስን ከሚያስነውርና ከሚያስነቅፍ ተግባር ንጹሕ ማድረግ ያስፈልጋል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሚ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "ከሕግ ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ በሕግም የዕውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ የዕውሮች መሪ በጨለማም ላሉ ብርሃን የሰነፎችም አስተማሪ የሕፃናትም መምህር እንደሆንህ በራስህ ብትታመን እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምር ምን? አትሰረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህ አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን፣ በእናንተ ምክንያት የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና" ይላል ሮሚ ፪· ፲፰—፳፬ ።

በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የማታውቃቸውና ያልላከቻቸው ባሕታውያን ነን ባዮች በየአብያተ ክርስቲያናቱ እናስተምራለን በማለት የሆነ ያልሆነውን ሲዘላብዱ ይሰማሉ እነዚህ ጉርፍ አመጣሽ ባሕታውያን መሰሎች ለቤተ ክርስቲያናችን ከሚሰጡት ጥቅም ይልቅ የሚያደርሱት ጉዳት የሚበልጥ መስሎ ስለሚገመት ከአድራጉታቸው መከልከል አለባቸው እንላለን ።

ለሁንም ቅድስተ ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ዲዮጋን መብራቷን አብርታ እምነታቸውን አጽንተው ሥነ ምግባራቸውን አሳምረው ከተንኮል ከክፋት ከምቀኝነት ርቀው ፍቅርን ሰላምን አንድነትን የሚያስተ ምሩ ምሁራንን አጥብቃ ትፈልጋለች ።



www.ethiopianorthodox.org

# ጥምቀተ ክርስትና

የሰው ዘር መጀመሪያ አዳም የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፉ ለመላው የሰው ዘር ክብሩ በውርደት ጽድቁ በኃጢአት በረከቱ በመርገም ተለውጦ ለአምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመናት ቆይቶአል ።

ከዘመኖቹ ፍጻሜ በኋላም አበው ነቢያት በተናገሩት መሠረት የመዳን የተሳሉ ጊዜ ሲደርስ በባሕርዩ ለውጥ በሥልጣኑ ሽረት የሌለበት የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅ/ድንግል ማርያም ተወለደ ዘመናትንና ጊዜያትን ያስገኘ ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ ዘመናት ተቆጥረውለት ሰላሣ ዘመን ሲሞላው በመጥምቁ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ውሃ ተጠመቀ።

"አሚሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ ከመ ይጠመቅ በፈለገ ዮርዳኖስ" ያን ጊዜም ጌታ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ውሃ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮሐንስ መጣ (ማቴ·፫·፲፫) ብሎ ቅ·ማቴዎስ እንደጻፈው ጌታ የሰውን ልጅ የኃጢአት መርገም ለመሻር ሲል በዮርዳኖስ ውሃ በተጠመቀ ጊዜ አብ በደመና ሁኖ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱ ሠመርኩ ወሎቱ ስምዕዎ የምወደው ልጄ እርሱ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ አሰምቷል ። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በጌታ ራስላይ አርፎአል በዚህም የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ተገልጿል ።

"እኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ አላ ከመ የሐበነ ሱታፌ ንጽሕ ጌታ የተጠመቀው ለእርሱ የሚረባው የሚጠቅመው ሁኖ አይደለም እኛ በእርሱ አምነን ተጠምቀን ልጅነትን አግኝተን ከጌታ ጋር አንድ ልንሆን ነው እንጂ ተብሎ እንተጻፈ እግዚአብሔር ሰው መሆኑን አምኖ የተጠመቀ ማንኛውም የሰው ልጅ ድህነትን ልጅነትን ያገኛል ።

ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በትርጓሜው ላይ ሲገልጹ "ውሃ ለወሰደው ፍለጋ የለውም በጥምቀት ለተሰረየ ኃጢአትም ምርመራ የለውም በማለት በትርጓሜያቸውም ላይ ያትታሉ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል ተብሎ በቅ ማርቆስ የተመዘገበውም ስለዚህ ነው (ማር·፲፮·፲፮)

"ዘኢተወልደ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ አይክል ይባእ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም (ዮሐ· ፫·፭) ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማየ ዮርዳኖስ ያልተወለደ ልጅነትን ድኅነትን አያገኝም በጽድቅ ፈንታ ኩነኔን በኃጢአት ሥርየት ፈንታ መርገምን ያገኛል እንጅ ።

ለዚህም ነበር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ሂዱና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኋችሁን ሁሉ አስተምሯቸው እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ·፳፰—፲፱—፳) በማለት የተናገረው ከጌታ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ቅዱሳን ሐዋርያት በመላው ዓለም ሄደው ወንጌልን አስተምረው አህዛብን እያጠመቁ ልጅነትን እንዲያገኙ አድርገዋል ።

በሐዋርያት ትምህርት የጸኑት ሠለስቱ ምዕትም ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየት ኃጢአት የኃጢአት ሥርየት በምትሆን በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ሲሉ ጥምቀት የማትደገም የማትተው መሆኗን በጸሎተ ሃይማኖት ወስነው ለትውልደ ትውልድ እንዲተላለፍ አድርገዋል ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀትን ከጌቱ ምሥጢራት አንዱ በማድረግ ለዘለዓለም ስታስተምር ትኖራለች ።

በዚህም በጌታ ትዕዛዝና በሐዋርያት ትምህርት መሠረት ጥምቀት የመንግሥተ ሰማያት በር መግቢያ መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ወንዶች እንደተወለዱ በ፵ ቀናቸው ሴቶችም በ፹ ቀናቸው ይጠመቃሉ በዚህም ክርስቲያናዊ ሥርዓት የኢትዮጵያ ኦ·ቤ·ክ· አባላት ጸንተው አንዲት ጥምቀት አንዲት ሃይማኖት ተቀብለው ለዘለዓለም ይኖራሉ ።

ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ የተወለድንበት የሁላችንም የልደት በዐል ስለሆነ እኛ ክርስቲያኖች በደስታና በፍቅር መልካም ሥራ መሥራት ልናከብረው ይገባናል ከ፲፱፹፬ ዓ/ም የጥምቀት በዐል እንኳን አደረሳችሁ ፡

መ/ኤፍሬም በየነ



# ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ያደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ ከቁጥር ፩፻፶፩ የቀጠለ ፡

በ፳፱/፭/፹፬ ዓ·ም ጉዞአቸውን ብፁዕነታቸው ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ወደ አለማጣ ደ/ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በመቀጠል ከቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ ካህናቱና ምዕመናኑ በከፍተኛ ድምቀት ከተቀበሏቸው በኋላ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው ጸሎት አድርገው ሕዝቡ ወደ ተሰበሰበበት መድረክ ወጥተው በጊዜው በነበረው ችግር ለሁለት ዓመታት ያህል ከምዕመናኑ ተለይተው በመቆየታቸው የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸው ትምህርት ሲሰጡ ቆዩና ሕዝቡን በቡራኬ አሰናብተው ቅዳሴ ካስቀደሱ በኋላ ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ አርፈው የሀገር ሽማግሌዎችን የሰበካ ጉባኤ አባላትንና ካህናትን የሰንበት ተማሪዎችን አንድ በአንድ ሲያነጋግሩ ቆይተዋል፤ በሰንበት ት/ቤት በኩል ስለቀረበው የመጤ ሃይማኖት ጉዳይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተው ካህናቱም የንስሐ ልጆቻቸውን ነቅተውና ተግተው እንዲጠብቁ አስገንዝበው ስብሰባው በጸሎት ከተዘጋ በኋላ ሊቃውንቱ ቅኔ አበርክተዋል ።

፴/፭/፹፬ ዓ·ም ብፁዕነታቸው ጉዞአቸውን ወደ ኮረም ከተማ ቀጥለው አቀበቱን ወጥተው ሲጨርሱ ከበሩ ላይ እንደደረሱ የሀገር ሽማግሌዎችና አረጋውያን ካህናት እንዲሁም የሰንበት ተማሪዎች ብፁዕነታቸውን ለመቀበል በግልቢያ መኪና በመሆን እየዘመሩ ድምቀት በአለው አኳኋን ተቀብለዋቸዋል ። ከዚያም ገና ኃያሉ ማርያም ሳይደርሱ የከተማው ሕዝብ ግራና ቀኝ በመሆን በእልልታና በሆታ ካህናቱ ደግሞ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በመዘመርና በማሸብሸብ ከቤተ ክርስቲያኑ እስከሚገቡ ድረስ ልባዊ የሆነ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ብፁዕነታቸውም ወደ ቤተ መቅደሱ ገብተው ጸሎት አድርገው ለማረፊያ በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ካረፉ በኋላ የአውራጃው ቤተ ክህነት ኃላፊ አጠር ያለ ሪፖርት አቅርበዋል። ከዚያም በመቀጠል መዘምራኑ ፈቀደ ይርዳዕ የሚለውን ግስ አሰምተው ለ፲፭ ደቂቃ ያህል በሽብሸባ ገልጸዋል የሰንበት ተማሪዎችም ኖላዊነ መጽአ ኀቤነ የሚለውን ዘምረዋል እያንዳንዱ ሊቃውንትም ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ድረስ ስሜታቸውን በጋለ ሁኔታ ገልጸዋል ከተጠቀሰውም ቅኔ መካከል ጉባኤ ቃና ሥልጣነ ክህነት ተክለ ሰው ትመግባለች አፍርታ ። ተከዚ ቄርሎስ ያጠጣታልና ጢት ማታ የሚል ነበር ። ከዚያም ሌላው ሕዝቡ ከፍተኛ ደስታ ስለተሰማው እያንዳንዱ እየተነሳ ግሥ በማቅረብ ያልተሳተፈ የለም ። እንዲሁም የኢህአዴግ ተጠሪ የሆኑት መምሬ ሞላ የተባሉት ። "እይቴ ሀለው እለይቤሉ ስቅልዎ ስቅልዎ በማለት የተሰማችውን ደስታ በዜማ አቅርበዋል በዚያን ወቅት የነበረው ሕዝብ ብዛት ልክ የጥምቀት በዓል አከባበርን ይመስል ነበር ። ከዚህ በኋላ በመልአከ ገነት ተስፋ ወ/አብርሃም ስለ ብፁዕነታቸው ከቦታው መገኘትና በአለፈው ችግር ወቅት ሀሊናቸው ከሕዝቡ ጋር እንዳልተለየ በመግለጽ ትምህርት ተሰጥቶ በመጨረሻውም ብፁዕነታቸው ሕማምኑ፣ ምንዳቤኑ ተሰዶኑ በማለት ተነስተው ሰፋ ያለ ትምህርት ከሰጡ በኋላ ሕዝቡን ለመባረክ ሲጀምሩ ለሁለት ዓመታት ያህል ናፍቆ የነበረው ሕዝብ የብፁዕነታቸውን መምጣት በጉጉት ሲጠብቅ የቆየውን መስቀል ለመሳም የነበረው ትንቅንቅ በጣም ያስገርም ነበር ብፁዕነታቸውም በሕዝቡ ተውጠው ያሉበት ቦታ አይታወቅም ነበር ነገር ግን በብዙ ጥረት ተፈልገው ከተገኙ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተው እንደገና በመስኮት ዘልቀው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከ፩ሺህ በላይ የሚሆነውን ሕዝብ በመስቀል ባርከው አሰናብተዋል ።

በ፩/፪/፹፬ ዓ·ም ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ብፁዕነታቸው አዲስ ወደ ተቋቋመው ኮረም አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ጸሎት ከአደረጉ በኋላ በ፩፻፶ ዲያቆናት ለ፳፫ ቀሳውስት የሥልጣነ ክህነት ማዕረግ ሰጥተው ከአበቁ በኋላ ሕዝቡ ወደ ተሰበሰበበት መድረክ በተዘጋጀላቸው ቦታ ከተቀመጡ በኋላ መልአከ ገነት ተስፋ ወ/አብርሃም "በልዎ ለእግ



www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ግሩም ግብርከ" በማለት ተነሥተው ትምህርት ሰጥተዋል ። ሌሎችም በየተራ እየተነሡ ቤቶች ጭምር ሳይቀሩ የተሰማቸውን ደስታ ከገለጹ በኋላ ብፁዕነታቸው ተነሥተው አዲስ ስለተቋቋመው ቤተ ክርስቲያን ምዕመናኑ አንድነታቸውን አጠንክረው በመታገል ቀደም ሲል የጤና ጣቢያ የነበረውን ቤት አሁን ለቤተ ክርቲያን መገልገያ እንዲሆን ማድረጋቸው በጣም ያስደሰታቸው መሆኑን ገልጸው ሰፋ ያለ ትምህርትና መመሪያ ሰጥተው ምዕመናኑን አንድ በአንድ ከባረኩ በኋላ ለማረፊያ ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ሄደው ትንሽ ከአረፉ በኋላ ወደኮረም ሀ/ማ ሄደው በችግሩ ምክንያት ተበታትነው የነበሩትን ኮሚቴዎች እንደገና ከየመሥሪያ ቤቱ ለዚህ መንፈሳዊ ተግባር አገልግሎት ይሰጣሉ የተባሉትን አባቶች አቋቁመው እንደአበቁ በጠቅላላ በወፍላ አውራጃ ውስጥ የሚገኙትን ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት በአካባቢው በሚገኘው መሰብሰቢያ አዳራሽ አሰባስበው ፥

፩/ ስለ ሰበካ ጉባኤ መቋቋምና መጠናከር

፪/ ስለ ቤተ ክህነት ሠራተኞችና ስለ ሰበካ ጉባኤ አባላት የሥራ ግንኙነት

፫/ ስለ አሥራት አከፋፈል

፬/ በገጠሩና በከተማው በአዲስ መልክ ስለተቋቋሙት የወረዳ ሰበካ ጉባኤ ነን ስለሚሉት አባላት ለየ አንዳንዱ ከቅዱሳት መጻሕፍት በመጥቀስ ሰፋ ያለ ትምህርትና መግለጫ ሰጥተው መድረኩ ለጉባኤው ተሳታፊዎች ተሰጥቶ ያላቸውን ሀሳብ ከአቀረቡ በኋላ ብፁዕነታቸው የቀረበውን ሃሳብ አንድ በአንድ ከተመለከቱ በኋላ የሰጡት መግለጫ እስከ አሁን ድረስ ቤተክህነቱ በአለፈው ችግር ምክንያት ቦታውን ለቆ በመሄዱ እናንተ ቤተ ክርስቲያናችሁንና ሃይማኖታችሁን ጠብቃችሁ መቆየታችሁ ከልብ የሚያስመሰግናችሁ ነው ብለው በወረዳ ደረጃ ተቋቁመው ሲሠሩ ለነበሩት ፲፮ አባላት የመጻሕፍ ቅዱስ ሽልማት በጉባኤው መካከል በብፁዕነታቸው እጅ ተሰጥቷል ። ከዚህ በኋላ ብፁዕነታቸው የሰጡት መመሪያ እንደሚታወቀው ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን የምትመራው ቅዱስ ሲኖዶስ በአወጣው በቃለ ዓዋዲው ሕግ መሠረት ስለሆነ ለወደፊቱም መሠረት ያለበት መመሪያውንና የቃለ ዓዋዲውን ሕግ ጠብቆ ስለሚሆን እስከአሁን ተቋቁመው በወረዳ ደረጃ ሲሰሩ የነበሩት አባላት የቃለ አዋዲውን ሕግ ተከትሎ ያልሄደ ስለሆነ የአውራጃው ቤተ ክህነት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ምርጫው ማዕከሉን ጠብቆ እንዲፈጸም በማለት ከገለጹ በኋላ ጊዜው የምሽት ጊዜ በመሆኑ የቤተ ክህነቱ ሠራተኞችና የሰበካ ጉባኤ አባላቶች በመመካከር የሥራ ድርሻቸውን በመያዝና በመመካከር እንዲሠሩ መመሪያ ሰጥተው ስብሰባው በጸሎት ተዘግቶ የስብሰባው ተሳታፊዎች ቅኔ አበርክተዋል ።

ከሰጡትም ቅኔ መካከል ዘአምላኬ በአለፈው የችግር ዘመን ጐመን ታጥቶ ነበረ ። አሁን ግን እንጀራ ቁርሎስ አደረ በኮረም ከተማ መሶብ አቀማመጧ ያማረ የሚል ነበር ።

በ፱/፱/፹፬ ዓ.ም ከሌሊቱ ፮ ሰዓት ሲሆን ብፁዕነታቸው ከአደሩበት ቦታ ተነሥተው ሀያሉ ማርያም ገብተው ከካህናቱ ጋር ማህሌተ ጽጌ ቆመው ካደሩ በኋላ በ፲፩ ሰዓት ለ፺፯ ዲያቆናት ለ፹፬ ቀሳውስት የሥልጣነ ክህነት ማዕረግ ሰጥተው የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት በመልአከ ተስፋ ወ/አብርሃም ሲመራ ቆይቶ እንደተፈጸመ ብፁዕነታቸው ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ በመሄድ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተው ለቤተ ክርስቲያናችን ቅን አገልግሎት ሲሰጡ ለቆዩ ፱ መዘምራን የመጽሐፍ ስጦታ ወይም ሽልማት ሰጥተው ሠርሆተ ሕዝብ ሆኗል ። ከዚህ በኋላ ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሄደው ለትንሽ ሰዓት ከአረፉ በኋላ ፮ ሰዓት ሲሆን ከኮረም ተነሥተው አላማጣ ሲደርሱ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችን ለማነጋገር ከት/ቤቱ ሲደርሱ ወጣቶች አባ አቡነ እያሉ እየዘመሩ ከተቀበሏቸው በኋላ ከሰንበት ት/ቤቱ ሊቀ መንበር አጭር ሪፖርት ቀርቦላቸዋል ።

ብፁዕነታቸውም ለቀረበላቸው ሪፖርት መልስና ጥያቄ አድርገው ሊሆን የሚገባውን በመግለጽ መመሪያ ሰጥተው ጉዞአቸውን በመቀጠል አላማጣ ደ/ገነት ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ካህናቱና ምዕመናኑ በዕልልታና በሆታ ከተቀበላቸው በኋላ ታቦተ ሕጉን ባርከዋል ። መልአከ ገነት ተስፋ ወ/አብርሃምም ለተሰበሰበው ሕዝብ እሀውየ ተፋቀሩ በምልአ ልብ ከሙ በማለት ተነሥተው ትምህርት ከሰጡ በኋላ መድረኩን ለብፁዕነታቸው ለቀዋል ። ብፁዕነታቸውም ተነስተው ኢትቅትል ነፍሰ በማለት ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተው ሲያበቁ የአካባቢው ሕዝብ የአለውን አዝመራና አትክልት



ለማስባረክ የሚያደርገው መሽቀዳደም በጣም የሚያስደንቅ ነበር ። ብፁዕነታቸውም ሕዝቡንም አዝመራውንም ባርከው ጉዞአቸውን ቀጥለው አዳር ዋጃ ደ/ፀሐይ ሥላሴ ስለሆነ ከቦታው ሲደርሱ ካህናቱና ምዕመናኑ በደስታ ተቀብለዋቸዋል ብፁዕነታቸውም ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተው በዚሁ ቦታ አዳር ሆኖአል ።

በ፲/፱/፹፬ ዓ.ም ብፁዕነታቸው ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን በእግር ወደ ደብረ ዘመዶ ማርያም ገዳም ሲያመሩ እግር መንገዳቸውን የ........ቅዱስ ጊዮርጊስ የሀቀልፍ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስን አብያተ ክርስቲያናት እየጐበኙና እየባረኩ ጉዞአቸውን ቀጥለው በልማድ ሲአል ሜዳ እየተባለ ከሚጠራው ሥፍራ ሲደርሱ ቦታው ታሪክ ያለበት ስለሆነ ሕዝቡ ተሰብስቦ ቦታውን እንዲባርኩለት ስለጠየቀ ብፁዕነታቸውም የሕዝቡን ጥያቄ በመቀበል ወደ ተባለው ቦታ ሄደው የቦታውን ታሪክ ካዳመጡ በኋላ ይህ ቦታ ከእንግዲህ ወዲህ ሲኦል ሜዳ መባሉ ቀርቶ ብሩክ ሜዳ ተብሎ እንዲጠራ በማለት ሰይመው ሕዝቡንና ቦታውን ባርከው ጉዞአቸውን በመቀጠል ልክ ስምንት ሰዓት ሲሆን ደብረ ዘመዶ ገዳም ሲደርሱ ካህናቱ ልብስ ተክህኖ ለብሰው በማሸብሸብ ምዕመናኑ በእልልታና በሆታ በደመቀ ሁኔታ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚህ በኋላ በገዳሙ ውስጥ የሚገኙትን አረጋውያን መነኮሳት በየቦታቸው እየተዘዋወሩ ካነጋገሩ በኋላ ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሄደው እረፍት ከአደረጉ በኋላ ከሌሊቱ ፯ ሰዓት ሲሆን ወደ ገዳሟ ቤተ መቅደስ ገብተው የአቡነ በርተሎሚዎስን ገድል ሲያስነብቡ አድረው ሲነጋ ለ፩፻፶፯ ዲያቆናት ለ፹፰ ቀሳውስት የሥልጣነ ክህነት ማዕረግ ሰጥተዋል ። ከዚህ በኋላ ለትምህርት መስጫ በተዘጋጀው መድረክ ላይ ተገኝተው የአቡነ በርተሎሚዎስን ገድል ለተሰበሰበው ሕዝብ እየተረጐሙ ከአሰሙ በኋላ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ የሚለውን በመተንተን ትምህርት ሰጥተው ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ወደ ሌላ አምልኮት መሄድ እንደሌለበት ገልጸው ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ሰባኬ ወንጌል ቄስ ለገዳሟ ዕርዳታ እንዲሰጥ ሕዝቡን በመቀስቀስ አስተምረዋል ሌሎችም የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ የእመቤታችን ስዕል በካህናቱና በምዕመናኑ ታጅባ እየተንጐራደደች ከተዘጋጀላት ቦታ ደርሳ በአራቱ ማዕዘን ተገልጻ ለህዝቡ ታይታለች በዚህ ጊዜ ሕዝቡ የተሰማውን ደስታ በእልልታ ገልጾአል ። በዚሁ ዕለትም ከብፁዕነታቸው በተሰጠው ትምህርት ለገዳሟ በእርዳታ የተገኘውን ገንዘብ ብር ፪ሺ፮፻፹፱·0፭ መሆኑ ታውቋል ይህ ከሆነ በኋላ ብፁዕነታቸው አቡነ በርተሎሚዎስ የተቀበሉትን ቃል ኪዳን አንድ በአንድ ከገለጹ በኋላ ቃለ ቡራኬ ሰጥተው ስዕለ ማርያሟ በመጣችበት አኳኋን ተመልሳ ወደ መንበረ ክብሯ እንደተመለሰች የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት በብፁዕነታቸው ሲካሄድ ቆይቶ ልክ ፲፡፲፭ ሲሆን ተፈጽሟል ።

በ፭/፱/፹፬ ዓ.ም ከጧቱ ፱ ሰዓት ስብሰባ እንዲደረግ ብፁዕነታቸው ባዘዙት መሠረት ምዕመናኑና ካህናቱ እንዲሁም መነኮሳቱ ጭምር በገዳሟ አውደ ምህረት ተገኝተው ስብሰባው ቀጥሎ ስምምነት የታጣበትና መለያየት የተፈጠረበት በምን ምክንያት እንደሆነ እንዲገለጽ ከተደረገ በኋላ በስብሰባው የተገኙት ምዕመናንና መነኮሳት ለእያንዳንዳቸው ያላቸውን ሃሳብ አቅርበዋል ። ዋናው ምክንያት ግን መነኮሳቱንና ካህናቱን እንዲሁም ምዕመናኑን ሊያለያያቸው የቻለው የጥቅም ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ ጉዳይ ብፁዕነታቸው ቋሚ መመሪያ ሰጥተዋል ማንም ሰው ቢሆን በዚህ አካባቢ የምትገኙ ሁሉ ገዳሟን አምናችሁ የተቀመጣችሁ ናችሁ የዚህ ገዳም ደግሞ ህልውናዋ ካልተጠበቀ የገዳሟ ሥነ ሥርዓት ካልተከበረ ማንም ሰው በዚህ ሊኖር አይችልም መለያየት ካለ መቅሰፍትም ይመጣል ስለዚህ የገዳሟ ህልውናና ክብሯ መጠበቅ ስላለበት በገዳሙ ውስጥ ሰበካ ጉባኤ አይቋቋምም የገዳሟ አበምኔት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መተዳደር ብቻ ነው አሁንም ለገዳሟ አበምኔት የሌላት ስለሆነ አሁኑ አበምኔት የሚሆነውን መምረጥ አለባችሁ ብለው በሰጡት መመሪያ መሠረት ምርጫው ተካሂዶ በሙሉ ድምጽ አባ ገ/ሥላሴ የተባሉት ለገዳሟ አበምኔት እንዲሆኑ ከተመረጡ በኋላ አበ ምኔቱን በውጭም ሆነ በግቢ የሚረዱ አባላት ስለሚያስፈልጉ ፫ አባላት እንዲመረጡ ተደርጐ ፫ አባላት ተመርጠዋል ከዚህ በኋላ በመካከላቸው ያለው ቅራኔ በሰላም ስለተፈታ ብፁዕነታቸው መመሪያና ምክር ሰጥተው ወደፊት ጭቅጭቅና ንዝንዝ እንዲሁም መለያየት እንዳይኖር ከአስገነዘቡት በኋላ ስብሰባው በጸሎት

(ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንዱ ሲሆን ቁጥሩም ከማይደገሙት ምሥጢራት ነው ስለዚህም በድንግልና ለኖሩ እንጂ ድንግልና ለሌላቸው ሥርዓተ ተክሊል አይፈጸምላቸውም ።

በመጨረሻም ጥያቄህ ዓሣ በጾም እየተበላ መሆኑን ገልጸህ አለመበላቱ በየሳምንቱ እሁድ ከመቅድመ ተአምር ጋር ቢነገር ምን ችግር አለ? ብለሃል ፡ ለዚህ ተግባር ቀሳውስቱ ከተባበሩ እሁድ እሁድ ለምእመናኑ ቢያስረዱ ደስ ይለናል ። ነገር ግን አስቀድመን ለቀሳውስቱ የምናሳስበው ፍት ነገ ፍትህ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፭ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እንዲመለከቱ ነው የዓሣን በጾም አለመበላት በሰፊው ስለሚያብራራ ዓውቀው ለማስረዳት ይችላሉና ።

# የመጀመሪያው ተአምር በሠርግ ቤት ዮሐ· ፪·፲፩

አንዳንድ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዕድገታቸውና እድላቸው ለአብነት የሚበቁ በምሳሌነትም የሚጠቀሱ ሀገሮች ነበሩ ፤ አሉም። ዛሬ በዓለማችን በሥጋዊ ሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ነገር ግን ከመንፈሳዊ ዕውቀትና ጥበብ የተራቆቱ መኖራቸውን ደግሞ እናውቃለን ተአምራታዊ ዕድል ገጥሞአቸው መንፈሳዊ በረከትን ያገኙ ሀገሮች (መንደሮች) በቅዱስ ወንጌል ተመዝግበው እናገኛለን ። ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን ቅፍርናሆም የመቶ አለቃው ብላቴና የተፈወሰባት ። ማቴ· ፰ ፡ ፭—፲፬ ። ጌርጌሴናን አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት በሽተኞች የዳኑባት ፤ ማቴ· ፰ ፡ ፳፰—፴፬ ። ናይን የአንዲት መበለት ልጅ ከሞት የተነሣባት ሉቃ· ፯ ፡ ፲፩—፲፯ ። ቢታንይ አልዓዛር ከሞት የተነሣባት ዮሐ· ፲፩ ፡ ፲፬ ። ወዘተ ሲሆኑ ፤ ከነዚህ በበለጠ ግን የመጀመሪያውና ተቀዳሚው ተአምር የተፈጸመባት መንደር) ቃና ዘገሊላ ትባላለች ። የተፈጸመባትም ታሪክ በዮሐ· ፪ ፡ ፩—፲፪ ያለው ነው ። በዚህም ተአምራታዊ ኃይል ውስጥ ሦስት ታላላቅ ትምህርቶችን እናገኛለን ። እነዚህም ።

፩ኛ) የድንግል ማርያም አማላጅነት

፪ኛ) የውኃ ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ

፫ኛ) የጋብቻ ክቡርነት ናቸው።

ስለነዚህም አጭር ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነውና በአጭሩ እንመልከት ።

የድንግል ማርያምን አማላጅነት በሚመለከት ቤተ ክርስቲያናችን የአማላጅነት ትምህርት አጥብቃ ታምንበታለች ። ከምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (በስተቀር ከሌሎች የምትለይበትም አንዱ ይህ የአማላጅነት ትምህርት ነው ያመነችበትም እንዲሁ በከንቱ ያለ መረጃ ተነሥታ ሳይሆን ከላይ በታሪኩ እንደተመለከተው "የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው ። ኢየሱስም አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አልኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም እንጂ አላት ። እናቱም ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው" (ዮሐ· ፪ ፡ ፫—፯) ከዚህ ላይ የተነገረውን ቃል ከታችም የተፈጸመውን ድርጊት ሳያስተውሉ አንዳንድ የዋሃን ሰዎች" አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?" በማለት ጌታ ምልጃዋን እንዳልተቀበለ ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ እርስዋ እራሷ ምልጃዋን እንደተቀበላት ስላረጋገጠች "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" በማለት ለአስተናጋጆቹ ትእዛዝ ሰጥታለች ። በዚህም መሠረት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከላይ እንደተገለጸው ተአምራታዊ ኃይሉን የሚፈጽበት ጊዜው ገና ሳይደርስ የእናት ምልጃም ትእዛዝም በመሆኑ ያለ ወቅቱ ይህን አስደናቂ ተአምር ሊፈጸም ችሏል ።" ከአንቺ ጋር ምን አለኝ" የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ በማቴ· ፰ ፡ ፳፱ የተጻፈውን ማነጻጸር ይቻላል። ይህም ማለት የአንቺን ፈቃድ ላልፈጽም ሥጋሽን ለብሻለሁን? ፈቃድሽን የማልፈጽምበት ከአንቺ ጋር ምን ጉዳይ አለኝ? ማለቱ እንጂ መናፍቃን እንደሚሉት አይደለም ።

እንግዲህ እዚህ ላይ መመልከት ያለብን ጉዳይ የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ርኅርኂተ ልብነትን ነው ። ድንግል ማርያም የተቸገሩትን ፤ ከችግራቸው ፤ የተጨነቁትንም ከጭንቀታቸው ነፃ የምታወጣቸው ምልጃዋ ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪዋ በተሰጣት የባለሟልነት ጸጋ ክብር የማሠራት ችሎታም እንዳላት ማወቅ ይኖርብናል። በወንጌላዊው ሉቃ· ፩ ፡ ፳፰ ፴፩ እንደተገለጸው ። የእመቤታችንየድንግል ማርያም ርኅራኄ ለሰው ብቻ ሳይሆን "ይምሕር ጻድቅ ነፈሰ እንስሳሁ" (ጻድቅ ሰው ለእንስሳው ነፍስ ይራራል ምሳሌ ፲፪ ፡ ፲) እንደተባለው ሁሉ ለእንስሳትም እንኳ ሳይቀር በተለይም ለውሻ ውኃ ቀድታ በጫማዋ እንዳጠጣች በታሪክ መጽሐፍ ተመዝግቦአል ። ስለዚህ ድንግል ማርያም ለፍጥረት ሁሉ በፍቅሯ ፍጽምት በመሆኗ ዛሬም ሆነ ለዘለ ዓለም አማላጃችን በጭንቅ ጊዜም ደራሻችን መሆኗን እንመን ።

ሁለተኛው ደግሞ የውኃውን ወደ ወይን ጠጅነት የመለወጡ ሁኔታ ነው ። ሁላችንም እንደምናውቀው በተፈጥሮ ሀልውና ያገኘ ማንኛውም ነገር ሁሉ ውላጤ (ለውጥ) የሚያሳየውን በምክንያት መሆኑ ግልጽነው ። ለምሳሌም ያህል ሕፃን ወደ ጕልማሳነት ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ወደ ሞት ፍሬም ፍሬ እንጂ በዚህ በወንጌሉ የተፈጸመው አስገራሚና አስደናቂው ተአምር ግን ውኃው ወደ ወይን ጠጅነት እንዲለወጥ እንደኛ ባህል ብቅል ጌሾ ማር ፡ ስኳር ወዘተ· ሌላም ኬሚካላ ማቴርቴ ያል ሳያስፈልገው ፡ በማቴርያል ከተሠራው የበለጠ ሆኖ መገኘቱን የቀመሱት ሁሉ አድንቀውታል ፡ ይህን አድናቆት ያተረፈውን የወይን ጠጅ ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር በሚያደርግበት ጊዜ ለልማዱ ነገሮችን ይናገር ምልክቶችንም ያደርግ ነበር ። ለምሳሌም ያህል አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ፤ እንዲሁም ሰባት እንጀራና ጥቂት ዓሣ አበርክቶ በመገበ ጊዜ ጸሎትና ምስጋና አቅርቦ ነበር ። ማቴ ፲፬ ፡ ፲፯—፳፪ ። ፲፭ ፡ ፴፪ ፴፰

በሌላው ተአምራቱ ደግሞ ደንቆሮውንና ከልታፈውን ሰው ሲፈወስ ጣቶቹን በጆሮዎቹ አስገብቶ ምራቁን እንትፍ በሎ መላሱን ዳሰ "ኤፍታሕ" በማለት እንደነበረ በማር ፯ ፡ ፴፪—፴፯ ።እንመለከታለን ። እንዲሁም ዓይነ ሥውሩን ሰው ዓይኑን ሲያበራ በዓይኑ ላይ ምራቁን ተፍቶ እጁንም ጭኖ እንደነበር በማር ፰ ፡ ፳፫—፳፯ ተጽፎ እናገኛለን ። በወይን ጠጅ ግን ከላይ የተጠቀሱትና ሌላም ምልክት ሳያስፈልገው "እስመ አልቦ ነገር ዘይስእኖ ለእግዚአብሔር" (ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና) ። ሉቃ· ፩ ፡ ፴፯ ። እንደተባለው በእርምሞ ብቻ ይህን አስገራሚና ዕፁብ ድንቅ የሆነ ተአምር ለመጀመሪያ ጊዜ መፈጸሙ ከሃሌ ኩሉ (ሁሉን ቻይ) መሆኑን አውቀን ሁሉንም ለእርሱ መተው አስፈላጊ እንደሆነ ያስተምረናል ።

ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ (ምሥጢረ ተክሊልን) የተከተለ ነው ። ይህ ምሥጢር ዓላማውና አስፈላጊነቱ በጣም ሰፊ ነው። ነገር ግን በአጭሩ እንመለከተዋለን ። በመሠረቱ የጋብቻ አስፈላጊነት በመጀመሪያ ዘር ለመተካት ፍትውትን ለማራቅ ሲሆን ፡ ለመረዳዳትና የተመላ ኑሮም ለመኖር አስፈላጊ ነው ። ዐላማው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጸጋ ክበር ለማግኘት ነው ። ሁለቱ ጾታዎች አንድ ከሆኑ በኋላ ልጅ ያገኛሉ ። ከቤተሰቦቻቸው ጋር ዝምድና ይመሠረታሉ ። ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ ነው ። መዝ· ፩፻፳፯ ፡ ፫ ። ባልና ሚስት በዚህ ዓለም በፍቅር እንደ ኖው እንደ ኖሩ ሁሉ በወዲያኛው ዓለም በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ አንድ ሆነው የእግዚአብሔርን ጸጋ ክብር ይጐናጸፋሉ ። ይህም ሥርዐተ ጋብቻ ያለ ዝሙትና ያለ ሞት በስተቀር የማይፈታ ሁሉ እንዳታመነዝር ምክንያት ይሆንባታል ፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ ይሆናል ። ብሎ አስተምሮአል ማቴ· ፭ ፡ ፴፪ ። ይህን ተከትሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል ። "ሚስት ባልዋ በሕይወት እስካለ ድረስ በጋብቻ ሕግ የታሰረች ናት ። ባልዋ ከሞተ በኋላ ግን የፈለገችውን ልታገባ ትችላለች ሆኖም የምታገባው ሰው ክርስቲያን መሆን አለበት ይላል (፩ ቆሮ· ፯ ፡ ፴፱) ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤት ተገኝቶ ተአምራታዊ በረከት የሰጠው እንዲህ ዓይነት ዓላማና ቁም ነገር ያለው በመሆኑ ነው ። እንግዲህ ከዚህ ታሪክ የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር አለ ። ቤተ ክርስቲያናችንም በየዓመቱ ጥር ፲፪ ቀን የምታከብረው ትምህርታዊና ተአምራታዊ ስለሆነ ነው ። ትምህርታዊነቱም ዛሬ የዘመናችን ትውልድ አብዛኛው ከሥርዓተ ጋብቻ ርቆ ስለሚገኝ ብዙ ችግር ስለገጠመው መመሪያ ይሆናል ። እንደሚታወቀው ሁሉ ትውልዱ ንጽሕናን ባለመጠበቁ ሥርዓተ ጋብቻንም ባለመፈጸሙ ምክንያት በተላፊው በሽታ በኤድስ እየተቀጣ ይገኛል ። የናቀው ንጽሕና የሸሸውም ሥርዓተ ጋብቻ ከእመቀ እመቃት ውስጥ ጥሎት ይገኛል ። ይህም ችግር የወይን ጠጅ ካለቀ





www.ethiopianorthodox.org

በት የሠርግ ቤት በእጅጉ የባሰ ችግር ነው ። ምክንያቱም የሕይወት ጉዳይ ነውና ። የሠርጉ ባሌቤት ያለቀበት ወይን ነበረ ። የዛሬ ሰው ግን ያለቀበት ክርስቲያናዊ ሥርዐት ፣ ምራላዊ ሕይወትና ቆራጥ ወኔ ነው ።

በሥርዓት ትዳር ለመሠረቱት ጌታ በረከቱን ለመስጠት ገና በሠርጉ ዕለት ጀመረ ። ይህም በረከት እስከ ሕየወታቸው መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል መሆኑን ያመለክታል ። ይህ ያልገባቸው ሰዎች ግን እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንደሚመራ ስለማያምኑና ስለሚጠራጠሩ የሚጨብጡት አጥተው ከትዳር ዓለም ርቀው ይቀራሉ ። ይህ እንዳይሆን ሕገ እግዚአርሔርን መጠበቅ ተገቢ ነው ።

በጋብቻ ዝግጅት ጊዜ እንደ ሌላው ዝግጅት ሁሉ መደረግ የሚገባው መጀመሪያ በካህን (በቄስ) አማካሪነት መጀመር በፍጻሜውም ማሰባረክ ተገቢ ነው ። ይህማ ባይሆን ኖሮ ጌታችን በሠርጉ ቤት ተገኝቶ ባልባረከም ፣ በረከትም ባልሰጠም ነበር ።

እንግዲህ በአጠቃላይ ይህ ዕለት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርቶስ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገበት ነውና ዛሬም ከሕጉና ከሥርዓቱ የራቀውን ዓለም ታርቆ ከታዘዘው መቅሠፍት እንዲሠውረው እንጸልያለን ።

ዲ/ቤዛ ዓለሙ

# የጊዜ ትግል

ከብፁዕ አቡነ አብርሃም
ሊቀ ጳጳስ

የትግል ዓይነቱና መልኩ የተለያየ ነው በዚህ ዓለም ያለ ሰው አራሽ ገበሬም ሆነ ነጋዴ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ የሚያደርጉት ትግልና ውጣ ውረድ የተለያየ መልክ አለው ለምሳሌ አራሹ ወይፈኑን አቅንቶ ቀንበር በመጫን አለማምዶ ከደንበኛው በሬ ጋር ይጠምድና ቀንበር አሳሳቡን ወደፊት እንጂ ወደኋላ እንዳይል ከነባሩ በሬ ጋር ያቆራኘዋል በዚህ ዓይነት የቀኑን ሐሩር የሌሊቱን ቁር ታግሦ በወቅቱ ዘር ይዘራል ፣ ወቅቱን ጠብቆ ሰብሉን አጭዶ ይከምራል ወቅቶም ያመርታል አምርቶም በጎታው በጎተራው ይከታል ያከማቻል "ያዕ.፭ቁ.፯ ነጋዴውም ትርፍ ለማግኘት አገር አቋርጦ ወንዝ ተሻግሮ ያመጣውን ዕቃ እንደጊዜው ዋጋ እየሸጠና እየለወጠ ንግዱን ያካሂዳል ። ሁለቱም በየበኩላቸው ኑሮአቸውን ለማመቻቸት ውጣ ውረዱን ሳይሰለቹ የኑሮ ትግል ያደርጋሉ ።

ሌላው ደግሞ የፖለቲካ የሙግት ትግል የሚያደርግ አለ ይኸውም በጽሑፍም ስለሚሆን እንደ ዘመኑ አነጋገር ቀዝቃዛ ጦርነት ይባላል ።

ሌላው ትግል ደግሞ ሁለት ሰዎች አንገት ለአንገት ገጥመው እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚያደርጉት ትግል አለ ይህም እንደ ያዕቆብ ትግል ማለት ነው ከሁለቱ አንዱን ከምድር የጣለው እንደ ሆነ ታግሎ ጣለ ይባላል "ዘፍ. ፴፪ ፳፬" ይህ ዓይነቱ ትግል የጉልበት ትግል ይባላል ፣

የጊዜ ትግል ግን ከዚህ ሁሉ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን ልዩነቱንም ከሐዋርያው ቃል መረዳት ይቻላል ደስ ይላቸው የነበሩት ደስ እንዳላለቸው የሚገዙም ምንም እንደሌላቸው በዚች ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንዳማይጠቀሙ ይሆናሉ ፣ የዚች ዓለም መልክ አላፊ ነውና ብሎአል ቆሮ ፯ ቁ. ፴፩ ፣

ጌታም ለዓለም ቤዛ ሆኖ በካህናት አለቆች እጅ የሚያዝበትን ጊዜ ለአይሁድ ጭፍሮች ሲያመለክት ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጎመድ ይዛችሁ መጣችሁን? በቤተ መቅደስ ዕለት ዕለት ከናንተ ጋር ስናር እጃችሁን አልዘረጋችሁልኝም ነበር ዛሬ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ጊዜ ሥልጣን ነው ብሎአቸዋል ሉቃ ፳፪ቁ.፶፫።

እምን ጊዜ ያነሣል ፣ ጊዜም ይጥላል ጊዜ ያነሣው ክፉ ሰው በተፈጥሮ መስሉ ሰው ላይ የፈለገውን ግፍና በደል ሊፈጽም ይችላል ጊዜ እንሥቶታል ባለጊዜም ነውና ለምን ይህን አደረግህ የሚል ተቃዋሚ የለውም የፈጸመውም ግፍና በደል ለእርሱ አይሰማውም መልካም ያደረገ መስሎ ስለሚታየው ምንም ስቅቅ አይለውም የሚገድላቸው ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል ተብሏልና።



በሌላ በኩል ደግሞ ጊዜ ያነሣው ደግ ሰው የሆነ እንደሆነ ቃሉ ተደማጭ ንግግሩ ጣፋጭ በመሆኑ በአካባቢው ሁሉ ታፍሮ ተከብሮ ይኖራል ። ምክንያቱም ጊዜውን ተከትሎ የጊዜውን ሁኔታ አጥንቶ እንደ ጊዜው አቋሙን አስተካክሎ ስለሚሠራ ከበላይ ባለ ሥልጣን ዘንድ ተወዳጅነት አለው ለምሳሌ ፣ ለዕብራዊው ዮሴፍ በፈርዖን ሕልም መነሻነት ያለበትን የጊዜውን ምቾትና ወደፊት የሚመጣውን የጊዜ አስከፊነት ከነመፍትሔው አብራርቶ በነገረው ጊዜ በንጉሡ ፈርዖን ፊት ፍጹም ባለሟልነት አግኝቶ በሕዝቡም ሁሉ ተወዳጅነትን አግኝቷል ዘፍ.፵፩ቁ.፳፰–፵፰

ነቢዩ ዳንኤልም አጋጣሚ ጊዜ አግኝቶ ንጉሡ ናቡከደነፆር ያየውንና ከባቢሎን ጠበብት የተሠወረውን ሕልም ለእርሱ ይገልጥለት ዘንድ ወደ እወነተኛው አምላክ እግዚአብሔር በ፫ ቀናት ሱባዔ በጠየቀ ጊዜ ንባቡ ከነምሥጢሩ ተገልጦለት አብራርቶ ለመተርጐም ችሎአል ፣ ይህንንም ለገለጠለት አምላክ ባቀረበው ምስጋና ገልጦታል ጥበብና ኃይል የእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ (ይመስገን) ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአዋቆች ይሰጣል የተደበቀውንና የተሠወረውን ይገልጻል ፣ በጨለማ ያለውን ያውቃል ፣ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው ዳን.፳፩– ፳፩–፳፫ ብሎአል ፣ በዚህም ምክንያት ንጉሡ ዳንኤልን ከፍ ከፍ አደረገው በባቢሎን አውራጃ ሾመው ፣ ከባቢሎን ጠቢባን ሁሉ በላይ ዋንኛ አለቃ አደረገው ይላል ዳን.ቁ.፵፰–፵፱ ይህ ሁሉ የጊዜ ትግል ውጤት ነው ለሁሉም ጊዜ አለው ተብሎአልና መክ ፫–ቁ.፪ ።

እንግዲህ በሰኮንድ በደቂቃና ሰዓት የሚቆጠር ጊዜን የሰጠ የሀብታት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው ስለሆነም በጊዜ ከራሳችን ጀምሮ ለአገር ለወገን የሚበጅ ጠቃሚ ሥራ እንሥራ ልንሠራበትም ይገባል ፣ ጊዜን ብንሠራበት በውጤቱ የሚያስደስተውን ያህል ባንሠራበት ራስን ያሳዝናል፣ ከበላይም ወቀሳን ያስከትላል ጊዜ በከንቱ ሲያልፍ ድምፅ አያሰማም ኰቴ የለውም ከልብ ላይ ጸጸትን ጥሎ ያልፋል እንጂ ስለዚህ በጊዜ እንጠቀም እንጂ እንለግም ፍሬውን በጠበቅነው ጊዜ እናገኘዋለንና (ገላ.፮ቁ.፲) ።

# ለኅብረተሰቡ እውነተኛ ፍቅር ያስፈልገዋል

እንደዘመናችን ዴሞክራሲ አባባል ሕብረተሰብ ማለት ኅብረ ብሔር ኅብረ ሰብ ሕዝብ በእውነተኛ ፍቅርና በሰላም ተስማምተው የሚኖሩ አንድ አካል ማለት ናቸው ። የአካልም ምሳሌ የተሰጠበት ዋናው ምክንያት በሰው አካል ውስጥ ያሉት ብልቶች ተባብረው ከሠሩ ጤናማ አካል ስለሚኖራቸው ሙሉ አገልግሎት ለመስጠት ይችላሉ ከመካከላቸው አንዱ ብልት ከታመመ ግን ሁሉም ታማሚ እንደሚሆኑ ለማንም የተሰወረ አይሆንም ።

ከላይ የጠቀስናቸውም ክፍሎች ተባብረው ከሠሩ አገሪቷም ሆነ እድገቷ ጤናማ ስለሚሆን በሁሉም ረገድ ከበርቴ ትሆናለች በፍቅር ተባብረው የማይሠሩ ከሆነ ግን ኢኮኖሚው ታማሚ ስለሆነ ውድቀት እንጂ እድገት የለም ይህንን በመጠኑ ዝርዝር አድርገን ያየን እንደሆነ ሕብረተሰቦች በየሙያቸው ወደ ሥራ ዓለም በሚሰማሩበት ጊዜ ካህናትም ሆነ ምእመናን አሠሪዎችም ሆኑ ሠራተኞች እረጂዎችም ሆኑ ተረጂዎች አስተማሪዎችም ሆኑ ተማሪዎችም ገበሬዎችም ሆኑ ነጋዴዎች በጠቅላላው ማንኛውም ሕብረተሰብ ብቻውን መኖር ስለማይችል በመካከሉ እውነተኛ ፍቅር እንዲኖር ሁሉም በየበኩሉ መጣር ይገባዋል ።

ክርስቶስ ስለፍቅር ጠቃሚነት ሲያስተምር በዮሐ.ም.፲፫፥፴፭ እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ ብሏቸው ነበር ። ደቀመዛሙርቱም እርስ በርሳቸው ስለተፋቀሩ ወንጌልን ተዘዋውረው በማስተማራቸው የተለያየውን ዓለም አንድ ሊያደርጉት ከመቻላቸውም ሌላ አልጫ የነበረውን ሕብረተሰብ በክርስቶስ ወንጌልና በእውነተኛ ፍቅር ሊያጣፍጡት ችለዋል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በ፩ኛ ቆሮ ም.፲፫ ቁ.፮–፲፫ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለአመጻ ደስ አይለውም ሁሉን ይታገሳል ፣ ሁሉን ያምናል ፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል ። በሁሉ ይጸናል ሲል በፍቅር በኩል የሚገኘውን መንፈሳዊ ስጦታ አስተምሯል ። በየጊዜው የተነሱ አያሌ ሊቃውንትም ስለፍቅር ተናግረ



www.ethiopianorthodox.org

ዋል ። ብዙ ድርሰትም ጽፈው አልፈዋል ።

ከእነዚህም መካከል በርትራንድ ራሰል የተባለው መንፈሳዊ ሊቅ ፩ኛ ፍቅር በተባለው መጽሐፉ በገጽ ፲፭ ሲጽፍ እውነተኛ ፍቅር በተፈቃሪ ሰዎች ልብ ውስጥ እንደ እሳት እየተቀጣጠለ ከመንደድ በቀር ምንጊዜም አይጠፋም ። በየጊዜውም እየጋለ ከመሄድ በቀር አንዳች ነገር አያቀዘቅዘውም ራሱን ስለሌላው ከሚያስቸግር በቀር ሌላውን ለራሱ አገልጋይ ለማድረግ አይሻም ሌላውንም ራሱን መስዋእት አድርጎ ያቀርባል እንጂ ሌላውን ለራሱ መስዋእት አድርጎ አይቀርብም በማለት ሐሳቡን ለአንባቢያን አካፍሏል ።

ይህንንም በአንዲት የልጅ እናት አድራጎት ልንረዳ እንችላለን ። አንድ ቀን የዚህችው ልጅ እናት ቤት በድንገት የእሳት ቃጠሎ ተነሳና ቤቷ በእሳት ተያያዘ እሷ ግን ለጊዜው አልነበረችም ጐረቤቶች እሳቱን ለማጥፋት ዙሪያውን ከበው ይታገሉ ነበር ከውስጡ ያለውንም እቃ ለማውጣት በተቻለ መጠን ይደክሙ ነበር ። በውስጡ አንዲት ሕፃን ልጅ ተኝታ ነበረች ። እነሱ ግን አላዩአትም ነበረ ። እናትየዋም እንደመጣች ዘላ ወደ እሳቱ ውስጥ ገባች ። ሕፃንዋንም ይዛ ለመውጣት ስላልቻለች ጐድጐድ ያለ ሥፍራ ፈለገችና ሕፃንዋን ከዚያ ውስጥ አስተኛቻት እሷም በላይዋ ላይ ተጋደመችላት ፤ እሳቱ ከጠፋ በኋላ እቃ ለመፈለግ የገቡት ሰዎች የሕፃን ድምፅ ሰሙ ጠጋ ብለው ቢመለከቱ እናትየዋን ተቃጥላ አራ ሲያገኟት ሕፃንዋን ግን በሕይወት አግኝተው አነሷት።

ይህንን የተመለከተ አንድ ክርስቲያን ሰው በሁኔታው እያለቀሰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለእኛ ኃጢአት ተላልፎ ነው እንደዚህ የሞተልን ። በኃጢአት እሳት ይቃጠል ከነበረው ዓለም ውስጥ ገብቶ ከእንዲህ ያለው የበደል ወላፈን ያዳነን ይነድ የነበረውንም የገሃነም እሳት በደሙ ያጠፋልን እያለ በጣም እያዘነ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሐዘኑን እንደገለጸ ይነገራል ።

ሰውዬውም እንዳለው እውነተኛ ፍቅር ይህ ነው ። ሰዎቹ ቤቱ ሲቃጠል ዙሪያውን ከበው ያዩ ነበር ሌላው ቀርቶ በቤት ውስጥ ያለውን እቃ እንኳ ለማውጣት አልደፈሩም እናትየዋ ግን ወደሚንቀለቀለው እሳት ውስጥ ሳትፈራ ገባች ስለልጇም ሕይወቷን ለወጠች እስከሞት ድረስ የሚከተል እውነተኛ ፍቅር ያስፈልገናል ።

ፍቅር ሁሉን አስተካካይና እኩልነትን ስለሚሰጥ ለሁሉም ልናዝን እና ልናገለግል ይገባናል ይህም በእያሪኮ በረሃ በዱላ ተቀጥቅጦ የወደቀውን መንገደኛ ያሳስበናል እንዲህ ያለውን ከርታታና ጥግ የለሹን በፍቅር አንስቶ ቁስሉን የሚያክመው ወዳጅ ያስፈልገው ነበር ። ቀና ርኅሩኅ ውሃ የሚያጠጣውና ምህረት የሚያደርግለት ፍቅረኛ ያሻው ነበር ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች እያዩ አልፈውት ሄደዋል ። ከነዚህም መካከል ፈሪሳውያን ካህናት ይገኙበታል እነሱም እዩ እናንተ ወንበዴዎች እግዚአብሔር ይይላችሁ አሁን ምን አደረጋችሁና ነው ይህን ያህል ደብድባችሁ ከዚህ ከበረሃ የጣላችሁት እያሉ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ከማለፍ በቀር እውነተኛ ፍቅራቸውን እንዳልገለጡለት ከሥራቸው መረዳት ይቻላል ። ርሕሩሑ ሳምራዊ ግን በዱላ ተቀጥቅጦ የወደቀውን በሽተኛ አንስቶ ቁስሉን አከመለት ። እስከ መጨረሻውም ድረስ እውነተኛ ፍቅሩን ገለጸለት ። ስለዚህ ማንኛውም ሕብረተሰብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንተም እንደዚሁ አድርግ ያለውን በተግባር ማዋል ይገባዋል ።

እኔና እናንተም እንደ ፈሪሳውያኖች በችግር አዘቅት ውስጥ የወደቀውን ሰው እያየን አንዳች ፍቅር የምናሳየው ከንፈራችንን እየመጠጥን የምናልፈው ከሆነ በእኛና በእሱ መካከል ከጭካኔ በቀር ፍቅር የለም ። ፍቅር በማጣት ብቻ ሁኔታው ተወስኖ አይቀርም ። እንዲህ ያለው ኑሮው የተሳቀለበት ሰው ካለማስተማሩና እውነተኛ ፍቅርን ካልገለጡበት የሥራ መንገድን ካላሳዩት የራሱን ሕይወት ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰላማዊ ኑሮ ይበክላል ። ስለዚህ አንዱን ወንድማችንን ማዳን አካባቢውን ሁሉ ማዳንና የብዙዎችን ሕይወት ማትረፍ ነው ።

አንዳንዶችን ግን ወንድማችንን ከማዳን ይልቅ ውንደማችንን በአሉባልታ መግደል ደስ ይለናል። ይኸውም ከመካከላችን ሲለይ እናማዋለን ። በሆነ ባልሆነው ስሙን እናጠፋለን ። በአጠገባችን ቢኖር ደግሞ እንደ አንተ ሥራ ወዳጅ ወንድም አፍቃሪ የለም እያልን እናወድሰዋለን ። እንዲህ ያለውም ክርስቲያናዊ ፍቅር ሣይሆን ሰይጣናዊ ፍቅር ነው ።



ባንታደል ነው እንጂ ፍቅር ለሁሉ የሚበቃ እና የሚያልቅ በረከት ነው ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን አባት የተባለው አውሳብዮስ እግዚአብሔር ፍቅር ነው በተባለው መጽሐፉ በገጽ ፵፪ ሲጽፍ ፍቅር በአዳራሽ ውስጥ ትልቅና ትንሽ አዋቂና መሃይምን በአንድ ገበታ ላይ ሳይለያዩ የሚመገቡበት በመሆኑ ፍቅር ቢመገቡት የማያልቅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ በረከት ነው ። ከዚህም የተነሣ ፍቅር ከሕይወት ማዕበል የምንድንበት ወደብ መልካሙን መንገድ የሚያሳይ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት የምንሸጋገርበት ድልድይና ከምድር ወደ ሰማይ የምንወጣበት መሰላል ነው ብሏል ።

ይህን የመሰለውን መልካም ዓላማ ተከትለው አንዳንድ ቅዱሳንም አገራቸውን ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ሕይወታቸውን መሥዋዕት ያደረጉት ሕብረተሰቡን በመደገፍ ጠቃሚ ውጤትን ለማግኘት የደከሙት ስለእውነተኛ ፍቅር መሆኑን ታሪካቸው ይመሰክራል ። በተጨማሪም አንዳንድ የወንጌል መምህራን ውብና ምቹ የሆነውን የተወለዱበትን ቤትና ንብረታቸውን የሚወዷቸውን ቤተሰቦቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ትተው ወደ ጨለማው ብሄረሰቦች ሄደው የወንጌልን ብርሃን እያበሩ ሰዎችን ወደ እውነት በመምራታቸው እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ የሚለውን መልካም ስም ያገኙ እጅግ በዙዎች ናቸው ።

አንዳንድ ሐኪሞችም በሕመም የሚሰቃዩትን ለመርዳት በየሀገሩ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ድካምና ችግር ይደርስብኛል ምቾት ይቀርብናል የሌሊት እንቅልፍ ያመልጠናል ሳይሉ በትእግሥትና በመልካም ፈቃደኝነት በሽታውን ድል እየነሱ ወገንን የሚያድኑት ለእውነተኛ ፍቅር ተገዢ በመሆናቸው ነው ። ምንም እንኳን በዚህ ዓለም የሰውን ልጅ የሚያገኙት በርካታ ችግሮች ቢሆንም ሁላችንም በየችሎታችን አቅማችን በፈቀደ መጠን ስለሰው ፍቅር አገልግሎት መስጠት ይፈለግብናል ።

በዚህ አንጻር እያንዳንዳችን ገንዘባችንንም ሀብታችንንም እውቀታችንንም ማካፈል የሚገባን ችግር ለሚበዛባቸው ለእንዲህ ያሉት ሰዎች ነው ። ካህናትም የሆን ኃጢአት እንዲወገድ ድንቁርና እንዲጠፋ ትምህርትና እውቀት እንዲስፋፋ የፍቅር መረብ መዘርጋት የሚያስፈልገንን ይህን የመሳሰለው ችግር በደረሰባቸው ሕዝቦች መካከል እየተገኘን የችግራቸው ተካፋይ የሆን እንደሆነ ነው ። ዛሬ ዓለም ሁሉ አተኩሮ በሰው ልጆች ላይ የደረሰውን የኑሮ ችግር ጨርሶ ከቁጥጥር ውጪ ሣይሆን በአጭር ለመቅጨት በሚጣጣርበት ጊዜ እኛ የልዩ ልዩ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ችግር ተቀጥቅጦ የወደቀውን ችግረኛ አንስተን ቁስሉን አክመን ምሕረት የማድረግ ተግባር ብናከናውን የደጉን ሳምራዊ ምሳሌ መከተላችን ነው ። የወገንም የዘመድም እውነተኛ ፍቅር የሚባለው ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ዜና አበው

በቤተ ክርስቲያናችን አካባቢ የሚገኙ አበው በርከት ያሉ ሲሆኑ በተለያዩ ስጦታዎቻቸው ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ ሐዋርያው ጳውሎስ “የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና ለዚያው መንፈስ እምነት ለአንዱም መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ ለአንዱም ትንቢትን መናገር ለአንዱም መናፍስትን መለየት ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጐም ይሠጠዋል ይህን ሁሉ ግን የአንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል” በማለት እንደገለጸው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከፈጣሪ በተሰጣቸው ጸጋ ለቤተ ክርስቲያናቸው ለሀገራቸው ለወገናቸው ያገለገሉና የሚያገለግሉ አበው መኖራቸው የሚታወቅ ነው ።

እግዚአብሔር ካልፈቀደ በተማሩት ትምህርት በጉልበትም ሆነ በገንዘብ ለማገልገል አይቻልም በእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ሁሉም ሊከናወን ይችላል በዚህ መነሻነት ለመግለጽ የምንፈልገው ስለ አንድ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው ስማቸው መምህር አበበ ይባላል ታሪካቸው የሚከተለው ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

<u>መምህር አበበ ገብሩ</u> በ1895
ዓ/ም በሸዋ ሀ/ስብከት ዝቋላ አቦ
ከቄስ ገብሩ ወልደ መስቀልና ከወ
ይዘሮ እህት አፈራሁ ተወለዱ ዕድ
ሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከዝ
ቋላ ገዳም ከነበሩት መምህር አባ
ዘመስቀል ፊደል መቁጠር ጀም
ረው ንባብ በማንበብ ዳዊት
ደገሙ ቀጠልውም በዚሁ ገዳም
ከነበሩት ደብተራ ገብረ ሕይወት
ገብተው ጸዋትወ ዜማን አጠና
ቀው ተምረዋል ።

ከዚያም ወደ ጎጃም ሀ/ስብከት
ሂደው ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ከመ
ምህር ውብሸት ዕንግዳ ቅኔ ከእነ
አገባቡና ከእነ ዕርባ ቅምሩ ተም
ረው ሲያበቁ ወደዋሸራ በመሄድ
ከመምህር ገብረ ማርያም የተማሩ
ትን ቅኔ በሚገባ አጥብቀዋል ፤
እንዲሁም ወደምጣ ቅዱስ ጊዮር
ጊስ በመሄድ ከመምህር ጌታሁን
ዘንድ በተጨማሪ ቅኔና የውዳሴ
ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጓ
ሜን ተማሩ ።

ከጎጃም ወደቤጌምድር በመሻ
ገር በጋይንት አውራጃ በምትገ
ኘው አኮረት ኪዳነ ምሕረት ከነበ
ሩት መምህር ዕንግዳየሁ ዘንድ
ቀደም ሲል ተምረውት የነበረ
ውን ፀዋትወ ዜማ ከመከለሳቸ
ውም ሌላ ድጓ በሚገባ ተምረ
ዋል።

መምህር አበበ ትምህርት የመ
ማር ፍላጐታቸው ገና ያላከተመ
በመሆኑ አቋቋም ለመማር ከጋይ
ንት ወደ ጎንደር ከተማ አመሩ ፤
ከዚያም ጎንደር በዓታ ከነበሩት
ትግሬ ክፍሌ አቋቋም ተማሩ በተ
ጨማሪም በዚሁ ከተማ ቂርቆስ
ከነበሩት መምህር አካሉ አቋቋ
ሙን በሚገባ ተምረው ለመምህር
ነት የሚያበቃ ዕውቀትን አግኝተ
ዋል ።

ከዚያ በኋላ በበዓታ ግብዝናን
ተሹመው ተሹመውም የግብዝና
ውን ሥራ እየሠሩና እያጠኑ ሰባት
ዓመት አገልግለዋል በእነዚህም
ዓመታት ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓ
ድን ቤተ ክርስቲያን እሁድ እሁ
ድና በየወሩ የዮሐንስ ዕለት (ወር
በገባ በ፬ ቀን) በማጠን አገልግ
ሎት ይሠጡ ነበር ከዚያም በኋላ
ቀሐ ኢየሱስን አለቅነት ተሹ
መው አስተዳድረዋል ።

በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም ጎንደር ዓቢየ
እግዚእን ተሹመው እስከ ፲፱፻፶
፲፬ ዓመት አገልግለዋል እንዲ
ሁም በ፲፱፻፶ ዓ/ም ጣና ቂርቆስን
ተሹመው እስከ ፲፱፻፶፭ ዓ/ም ሠር
ተዋል ቀጥሎም ሰሜን እንዚራራ
ተክለ ሃይማኖትን ተሹመው አገ
ልግለዋል ። ከዚያም በኋላ ወደ
ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው
ከ፲፱፻፶፮ እስከ ፲፱፻፶፯ ዓመት
ድረስ ዝቋላ ገዳምን ተሾመው
አገልግለዋል እንዲሁም
ከ፲፱፻፷፩-፲፱፻፷፯ ዓ/ም አቲሳ
ተክለ ሃይማኖትን ተሹመው በቅ
ንነት አስተዳድረዋል ።

መምህር አበበ ገብሩ በጠቅላላ
ከ፲፱፻፳፯ ዓ/ም ጀምረው ቤተ ክር
ስቲያንን በግብዝና በዕልቅና አገ
ልግለዋል በጠቅላላ ሃ፳ ዓመት
ሙሉ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ቤተ
ክርስቲያንን በቅንነት ሲያገለግሉ
ኑረው ከ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ወዲህ ለመ
ሥራት ለመውጣትና ለመውረድ
ጉልበታቸው ስለደከመ በጡረታ
ሆነው በጸሎት ተወስነው እግዚአ
ብሔርን በማመስገን ላይ ይገ
ኛሉ።

መምህር አበበ ገብሩ አሁን የ፺
ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ ናቸው
መናኝ መነኩሴ እንደመሆናቸው
መጠን የሚረዳ ልጅ የላቸውም
የሚረዱት በወር በሚያገኙት ብር
፶ ነው የአበል ጭማሪ ለመጠየቅ
መጥተው እንዳነጋገርናቸው የም
ግብና የልብስ እጦት እንዳለባ
ቸው ገልጸው እኔ አሁን የምጨነ
ቀው ራበኝ ጠማኝ ታረዝኩኝ በማ
ለት አይደለም ሀገራችን ሰላም
ከሆነችልን የጐደለብኝን ቤተ ክር
ስቲያናችን እንድምታሟላልኝ
አልጠራጠርም ፤ ግን ሌት ከቀን
የማስበው ፤ የምጨነቀው የማዝነ
ውና የማለቅሰው ስለሀገራችን
ሰላም ነው ብለዋል በመቀጠልም
አሁን ዕድሜዬ ፺ ዓመት መሆኑ
ነው ወደፊት አምላክ ይጨምር
ልኝ ወይስ ይኸው በቃህ ይለኝ
እንደሆነ አላውቅም ግን አንድ
ቀንም ይሁን ሳምንት ወይም
ዓመት ይሁን ከዚያም በላይ እኖር
እንደሆነ የሚያውቀው አምላክ
ነው እንጂ እኔ አይደለሁም እስከ
ዚያው ድረስ ግን ስለሀገራችን
አዘውትሬ እግዚአብሔርን እለም
ናለሁ ፤ እናንተም መጸለይ አለባ
ችሁ ብለውናል ።

በዕርግጥ ስለሀገሩ ስለወገኑ የማ
ይጸልይ የማያስብ የማይጨነቅ
በአሁኑ ጊዜ አለ ተብሎ አይገመ
ትም ካለ ግን አንስሳ እንጅ ሰው
ነው ተብሎ አይገመትም ።

ሊቃውንቱ አዛውንቱ ትንሹ
ትልቁ በኅብረት ሆነው አቤቱታ
ቸውን ማቅረብ ያለባቸው ወደ
እግዚአብሔር ነው ሽማግሌ የሚ
ረዳው ሕፃናት የሚያድኑት የተራ
በው የሚጠግበው በሽተኛው
ታሞ ለማዳን የሚችለው በሀገር
ላይ ሰላም ሲሰፍን ነው ከላይ
ስማቸው የተጠቀሰው አባት የሚ
ኖሩት በድሎት ሳይሆን በችግር
ነው ግን የራሱ ችግር ይቅደም
አላሉም በሀገር ሰላም ከወረደ ችግ
ራቸው እንደሚወገድላቸው በማ
መን በመጀመሪያ የተመኙት ለሀ

(ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል)



# የግሸን ማርያም ታሪክ በአጭሩ

## ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የወሎ ሀገረ ስብከት ሊ.ቀ ጳጳስ

ግሸን ማርያም የምትገኘው በደ
ቡብ ወሎ በአንባሰል አውራጃ
ነው ። የአካባቢው ስም ግሸን
የገዳሙ ስም ደብረ ከርቤ ይባ
ላል። ይህች ቦታ በአንባ ላይ ያለች
አንድ በር ብቻ ያላት አራት ማዕ
ዘን የሆነች ቦታ ናት ። ስለዚህ
ነው ዓፄ ዘርአ ያዕቆብን አንብር
መስቀልየ በዲበ መስቀል ያላ
ቸው።

ንጉሡ ዘርአ ያዕቆብ ዓራት
ማዕዘን ያለው ተራራ ለማግኘትና
ግማደ መስቀሉንም በዚያ ለማ
ኖር ለብዙ ዓመታት ደክመዋል።
ግሸን ሲደርሱ ግን የተነገረላቸ
ውን ቦታ እንዳገኙ ምልክት ተሰ
ጣቸው ፡ ምክንያቱም ከሌሎች
ተራሮች ሲደርሱ ይንቀጠቀጡ
ነበር ። ከዚህ ቦታ ሲደርሱ ግን
መሬቱ ቀጥ አለ ። በዚህ ሁኔታ
በ፲፬፻፴፬ ዓ/ም የነገሡት ዓፄ
ዘርአ ያዕቆብ አምልኮ ጣዖትን
ከምድረ ኢትዮጵያ ጨርሶ ለማጥ
ፋት የታገሉትና ብዙውኑም ያጠ
ፉት እንደቆስጠንጢኖስ መፍቀሬ
አምላክ የተባሉት ከዚያ ዘመን
ጀምሮ ነው ።

ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ በዘመናቸው
ግሸን ላይ የእግዚአብሔር አብን
ቤተ መቅደስ አሳንፀው መስከረም
፳፩ ቀን ቅዳሴ ቤቱን አክብረው
ግማደ መስቀሉንም በዚሁ ቦታ
አስቀመጡ ። ስለዚህ ይህ ቦታ
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዓለ ታሪክ ፡
በዓለ ቃል ኪዳን ሆኖ በዚህ ምክን
ያት መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስ
ቲያን እንዲሁም የውጭ ቱሪስ
ቶች መስከረም ፳፩ ቀን በየዓመቱ
ከቦታው እየተገኙ በታላቅ ድም
ቀት በዓሉን ያከብራሉ ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሀገራ
ችን ላይ የውስጥ ጦርነት ይካሄድ
ስለነበረ ለሁለት ዓመታት ያህል
ሕዝበ ክርስቲያኑም ሆኑ የውጭ
ሀገር ቱሪስቶች ከመምጣት ተከል
ክለው ነበረ ኢ.ሕ.ዴ.ግ ሀገሪቱን
በመላ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ
አመራሩን ከያዘ ወዲህ በ፲፱፻፹፬
ዓ/ም መስከረም ፳፩ ቀን ሁሉም
ከአሉበት በመምጣት በዓሉ እንደ
ጥንቱ ለማክበር ችሏል ። ይህም
ሊሆን የቻለው ፩ኛ ደረጃ እየሸሸ
ሲወጣ በየመንገዱ የቀበረውን
ፈንጅ አዲስ አበባ ድረስ በመላ
ላክ ፈንጂውን የሚያወጡ ባለሞያ
ዎች ተልከው በደሴ ከተማ በአስ
ተዳደር ላይ ከሚገኙት የኢ.ሕ.ዴ.ግ
ወንድሞች ጋር በመሆን በአደረ
ጉት ከፍተኛ ጥረት ፡

፪ኛ በደሴ ከተማ የሚገኙት
የገጠር ፕሮጀክት ባለ ሥልጣኖ
ችና የቀን ሠራተኞች ባደረጉት
ከፍተኛ ትብብር ፫ኛ በኮምቦልሻ
ከተማ የሚገኘው የአውራ ጐዳና
መሥሪያ ቤት መሣሪያዎችንም
ሆነ ሠራተኞችን በማሳለፍ ሌት
ከቀን በመሥራት በ፲ ቀናት ፲
ኪሎ ሜትር መንገድ በመሥራት
ፈንጅና የውኃ ማዕከል እንዲሁም
በልዩ ልዩ መሣሪያዎች ተበላሽቶ
ለሶስት ዓመታት ያህል ከአገልግ
ሎት ውጭ አድርጐት የነበረውን
መንገድ በአጭር ጊዜ ውሀ አስመ
ስለው በመሥራታቸው ለተሳላሚ
ዎች ሁሉ እጽፍ ድርብ ደስታ
ተሰምቷቸዋል ። ጽሑፍ አቅራቢ
ከዚህ ላይ ጨብጨባ ነበር በጽ
ሑፍ አይጨበጥም እንጂ ይላሉ ።

በሥራው ላይ ደርሽ ስለአየኋ
ቸው በጣም የሚያስደስት ነበረ
ከዚህ ሁሉ በፊት የቅስቀሳ ዝግ
ጅት ነበረ ሊ.ቀ ሊቃውንት ተክለ
ማርቆስ የግሸን (የደብረ ከርቤ)
አስተዳዳሪ የሆኑት ፲፰ ኪሎ
ሜትር መንገድ በበቅሎና በእግር
እስከ ደሴ ከተማ በመምጣት በየ
መሥሪያ ቤቱ ባደረጉት ጥረት
በወሎ ሀገረ ስበከት ከ፵ ዘመናት
በላይ አገልግሎት የሰጡ ማለት
ስብከተ ወንጌልን በመስበክ ቤተ
ክርስቲያንን በማሠራት ልዩ ልዩ
ዛፎችን በመትከል ሕዝበ ክርስቲያ
ኑን በመቀስቀስ ያልተቆጠበ አገ
ልግሎት ሰጡ ፤ አሁንም በመስ
ጠት ላይ የሚገኙ በአባ መፍቀሬ
ሰብእ ፫ኛ በደሴ ከተማ የሚገኙ
በየአድባራቱ ባደረጉት አስተዋ
ጽኦ ሲሆን ለዚህ መልካም ተግ
ባር የተቃና እንዲሆን የሀገረ ስብ
ከቱ ሊቀካህናት በየመሥሪያ ቤቱ
እየሄዱ ባደረጉት ጥረት ነው ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መሥ
ሪያ ቤቶችና ግለ ሰቦች በተደረ
ገው የሥራ ቅንብር ፲ ኪሎ ሜትር
መንገድ ተሠርቶ ተሳላሚው
ሕዝብ ከቦታው በመገኘት የኃጢ
አት ሥርዩት እንዲያገኝ መልካም
አገልግሎት አበርክቷል ፤ በጉልህ
የታየው መልካም ፍሬ በዕለቱ
የተገኘው አስተዋጽኦ ሙዳየ ምጽ
ዋት ምስክር ነው ሕዝብ ክርስቲ
ያኑ ደስ ስላለውና ምኞቱም የተፈ
ጸመለት ስለሆነ በዕለቱ የተገኘው
ገንዘብ ብር ፵፯ሺ...
...ማንቲም ሆኖአል ፤ ይህ ...
ሊገኝ የቻለ...
ጸው በተደረገው መል...

(ወደ ገጽ ፲፯ ...)



www.ethiopianorthodox.org

# እንግዶችን ለመቀበል ትጉ

እንግዳ ማለት ታይቶ የማይታወቅ መጥቶ የማያውቅ ፡ ሰው ነው። ከሌላ ወገን ወይም አገር የመጣ እንግዳ ይባላል በብሉይ ኪዳን እንግዳ ሰው ፋሲካን ለመብላት ፡ ዘጸ· ም ፡ ፲፪ ቁ· ፵፫ ወደ ቤተ መቅደስ ለመግባት ፡ ሕዝቅ· ም· ፵፬ ቁ ፱ ንጉሥ ለመሆን ፡ ዘዳግ· ም· ፲፯ ቁ ፲፭ በጋብቻ ከእስራኤል ጋር ለመቀላቀል አይችልም ነበር ። ዘጸ· ም· ፴፬ ቁ· ፲፪—፲፯ ።

ነገር ግን ሕግን ቢቀበልና ቢገረዝ እንደ አገር ልጅ ይሆናል ። ዘጸ· ም· ፲፪ ቁ· ፵፰ በአዲስ ኪዳን ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነው ሰው እንግዳ ይባላል ። ኤፌ· ም· ፪ ቁ· ፲፩ እንዲሁም ክርስቲያን በዚህ ዓለም እንግዳ ነው ። ዕብ· ም· ፩ ቁ· ፲፫—፲፯ ።

እንግዶችን መቀበል በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ታዟል ። ዘሌ· ም· ፲፱ ቁ· ፴፫—፴፬ ሮሜ· ም· ፲፪ ቁ· ፲፫ ፩ኛ ጴጥ· ም· ፬ ቁ· ፱ ፡ እንግዳ እስከሚሄድ ድረስ ባለቤት ለእርሱ ኃላፊ ነው ዘፍ· ም· ፲፱ ቁ· ፩—፰ ፡ መሳ· ም· ፲፱ ቁ· ፩—፳፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍርድ ቀን ከሚናገራቸው ዓበይት ነጥቦች አንዱ እንግዳ ተቀባይነት ነው ። ማቴ· ም· ፳፭ ቁ· ፴፭ ፡ ፴፰ ፵፫ ።

በዚህ መሠረት እንግዳ መቀበል እንዴት እንደሆነ ለመጠቆም ያህል ፡ እንግዳ ሲመጣ "ቤት የእግዚአብሔር ነው ፡ ግባ ብሎ ተደስቶ መቀበል ፡ እግሩን ማጠብ፡ ከዘወትሩ ለየት ያለና ለእንግዳው የሚሆን ምግብና መጠጥ አዘጋጅቶ መመገብ ፡ የራስን መኝታ ለቆ እንግዳውን ማስተኛትና የመሳሰሉትን በጎ ሥራዎች መፈጸም ተገቢ መሆኑን ማስታወስ የሁላችንም ተግባር እንደሆነ መገንዘብ ያሻል ።

እንግዳ መቀበልን እንደ ቋሚ ሥራቸው አድርገው ይዘውት የነበሩትን አባቶቻችንን ለማስታወስ ወደኋላችን መለስ ብለን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናገላብጥ ልዩ የእንግዳ መቀበል ፍቅር የነበረውን ታላቁን አባት አብርሃምን እናገኛለን ።

የእስራኤል ዘሥጋና የእስራኤል ነፍስ አባት የሆነው አብርሃም በእግዚአብሔር እንደበት ተጠርቶ ፡ ከዘመድ አዝማድ ርቆ ፡ በምድረ ከነዓን በሚኖርበት ወቅት የዕለት ተግባር አድርጎ ይዞት የነበረው ዋና ሥራ ፡ የወጣ የወረደውን ፡ ያለፈ ያገደመውን መንገደኛ ተቀብሎ አብልቶ አጠጥቶ ፡ የሚያድረውን አሳድሮ ፡ የታመመውን አድኖ ፡ ለመንገዱ የሚያስፈልገውን አሟልቶ እንግዳውን ይሸኝ እንደነበረ ከግል የሕይወት ታሪኩ መረዳት እንችላለን።

ከዕለታት አንድ ቀን ማለትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፲፱፻ ዓ·ዓ አካባቢ ከትውልድ ሀገሩ ከዑር ተጠርቶ ወደከነዓን ከመጣ በኋላ በዚያ በነበረበት ዘመን ሁሉ ቤቱ ድንኳን ከመሆኑም በላይ ለመቀመጫ የሚሆነውን አካባቢ በመረጠ ጊዜ በየቦታው ለእግዚአብሔር መሠዊያ ይሠራ እንደነበረ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ። በተለይም መምሬ የተባለው አሞራዊው ወዳጁ በሰጠው ቦታ ላይ በነበረበት ወቅት በታላቁ የአድባር ዛፍ ሥር እንግዶችን ተቀብሎ ወደ ድንኳኑ በማስገባት አስፈላጊውን መቀበያና መስተንግዶ አድርጎላቸው እንዳበቃ የእንግድነት ጊዜያቸውን ፈጽመው ከቤቱ ሲወጡ ሦስቱም በበረከታቸው እንደባረኩትና ርስትን የሚወርስ ወንድ ልጅ ከሚወዳት ሚስቱ ከሣራ እንደሚወልድ የምሥራች ካሉት በኋላ የወንድሙ ልጅ ሎጥ ተቀምጦበት ስለነበረችው ከተማ ስለሰዶምና ገሞራ ኃጢአት መብዛት ስለጥፋቷ ከእንግዶቹ ጋራ በሰፊው ተወያይቶበታል ፡ በመጨረሻም ከተማይቱ ጥፋት እንዳይመጣባት የበኩሉን ጥረት አድርጓል። ዘፍ· ም· ፲፰ ቁ· ፩ ፍጻሜ።

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው እነዚህ ሦስት እንግዶች የተባሉት በማቴዎስ ም· ፫ ቁ ፲፯ እና ማቴ ፳፰ ቁ ፲፱ ፳ የሦስትነትና የአንድነት ስማቸው በትክክል የተገለጸው ቅድስት ሥላሴ መሆናቸውን ሁላችንም የምናውቀው ፡ የምንረዳውና የምናምንበትም ነው ።

ቅድስት ሥላሴ ከአብርሃም ቀደም ሲል በምድረ ሰናዖር ሜዳ የሰው ልጆች በአመፅ ያነፁትን የባቢሎን ሕንፃ ወርደው አይተው፡ የሰዎቹን አለመታዘዝና እንግዳ ለመቀበል የነበራቸውን ደካማ አመለካከት ተመልክተው ሕንፃውን በማፈራረስና ቋንቋቸውን በመደባለቅ እንደ ቀጧቸው ዘፍ· ም· ፲፩ ቁ· ፩—፱ ተዘግቦ እናገኛለን።

እንደገናም በአዲስ ኪዳን ዘመን ብዙዎች እንግዶችን ይቀበሉ ፤ የሚያስፈልጋቸውንም ያደርጉ እንደ ነበረ ከቅዱስ መጽሐፍ ስንረዳ ከእነዚህም የአዲስ ኪዳን እንግዳ ተቀባዮችና አክባሪዎች ፩፻፳ው ቤተሰብ ይገኙበታል ። የሐ·ሥራ ም· ፩ ቁ· ፲፭ ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አባባል ውኃ ከመፍሰስ ነፋስ ከመንፈስ እንደማያቋርጥ ፡ ቅዱስ ቅዱስ እየተባሉ ከሚመሰገኑት ከሦስቱ አካላት አንዱ ቅዱስ እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም በመጣበት ጊዜ የገዛ ወገኖቹ እንዳልተቀበሉት ፤ ለተቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን ሥልጣን እንደሰጣቸው በዮሐንስ ወንጌል ም· ፩ ቁ· ፲፩—፲፪ በግልጽ የምንረዳው ነው ።

በምድረ እሥራኤል ይኖሩ የነበሩት ዕብራውያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንቀበልህም ብለው ከነጭራሹ "ይሙት በቃ" ብለው ፈርደው እየተዘባበቱ እና እየቀለዱ ሰቅለው ገድለውታል ፤ እርሱ ግን በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል ተለይቶ ተነሥቷል ። እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብርሃም ቤት ባደረገው ድንቅ ተአምር መሠረት አሁንም በዮሐንስ ወ· ም· ፲፫ ቁ· ፩—፳ እንደተገለፀው ደቀ መዛሙርቱ ለመንግሥተ ሰማያት እንግዶች እንደመሆናቸው ራሱን ዝቅ አድርጎ ፡ እግራቸውን አጥቦ ሲያበቃ እንግዳ መቀበል እንዴት እንደሆነ ሲያስረዳቸው ።" እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ ትተጣጠቡ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ" ብሎአቸዋል ።

ታድያ ዛሬ በዘመናችን ይህ የእንግዳ አቀባበል ሁኔታ ምን ይመስላል ? በተለይም በዚህ በያዝነው ምዕት ዓመት በየአህጉሩ የፖለቲካ ውዝግብ ፡ ረሀብ ፡ ድርቅ ፡ ቸነፈር ፡ አገር ጥሎ ቁርበት አስጠቅልሎ ፡ ቤት አስፈርሶ ፡ ንብረት አስተኩሶ የሚያባርራቸው ደቂቀ አዳም ብጣት ከመቆጠር ካለፉ ዓመታት እየተደጋገመ ነው ። ስለዚህ አዕምሮ ያለን አዋቂዎች ነን ክርስቲያኖች ነን የምንል ሁሉ ተንኮልን ክፋትን ምቀኝነትን ትተን እንደ ታላቁ የሃይማኖት አባታችን እንደአብርሃም የወገኖቻችንን ችግርና ስቃይ ብንካፈል አብርሃም ድንኳኑን በእንግድነት የመጡት ቅድስት ሥላሴ ወደ እኛም ቤት የማይመጡበት ምክንያት ባለመኖሩም በኋላም ጌታችን ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል ፡ ወዳዘጋጀሁላችሁ መንግሥተ ሰማያት ትገቡ ዘንድ የአባቴ ብሩካን ወደ እኔ ኑ" የሚለውን የምሥራች ቃል እንደሚያሰማን ጥርጥር የለውም ።

እንግዲህ ሁላችንም አገር ፡ ወገን ፡ ዘመድ ፡ የሌላቸውን እንግዶች በመቀበል እየተጋን በየዓመቱ ሐምሌ ፯ ቀን የሚከበረውን በተለይም የአብርሃሙ ሥላሴ በመባል የሚታወቀውን ታላቁን በዓላችንን ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጋር ቅድስት ሥላሴን ወደየቤታችን በመጋበዝ በታላቅ ደስታ ማክበር ይገባናል ።

ቀሲስ ምሕረት ዘውዱ

# ዜና ሊቃውንት

## የመሪጌታ ተሠራ አየለ አጭር የሕይወት ታሪክ

መሪጌታ ተሠራ አየለ ከአባታቸው ከአቶ አየለ አገኘሁና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሠራዊት በሸር በ፲፱፻፳፬ ዓ/ም ኅዳር ፫ ቀን በወሎ ክፍለ ሀገር እሽትን ማርያም ደብር ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በተወለዱበት ደብር ከመምህር መልከ ጼዴቅ ፊደል ቆጥረው ንባብና ዳዊት ጾመ ድጓ መዕራፍና የቃለ ትምህርት ተምረው የቂቁና ሥልጣንን ተቀበሉ ።

ከዚያም ወደግዳን ወረዳ ሔደው እየላ ቅዱስ ሚካኤል ቅኔ መምህርነት ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ቀጸላ ቅኔ ከእነአገባቡ ከ፰ ዓመት በላይ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ። ሊቁ መሪጌታ ተሠራ ይህ የቅኔ መምህርነት ሞያ ይበቃኛል ሳይሉ ወደ አማራ ሳይንት ሔደው በተድባበ ማርያም ደብር በድጓ መምህርነት ከታወቁት ሊቅ ከእርሰ ደብር አክሊሉ ድጓና ዝማሬ መዋሥዕት ተምረዋል ። ከዚህ በኋላ ወደግሸን ማርያም ደብር ሔደው በመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ በመምህርነት ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ዶርጋ ዘንድ የመጻሕፍት ነገሥትን ትርጓሜ በሚገባ ተምረው ተመርቀዋል ።

ከዚያም ወደዋግ ሰቆጣ ሔደው በአቋቋምና በድጓ መምህርነት ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ዓለሙ ገብሩ ዘንድ አቋም እየተማሩ በትርፍ ጊዜአቸው ከማሕሌት እየተገኙ ቅኔ የሚቀኙትን መምህራን እየነጠቁና እያረሙ ስለታወቁ እርሳቸው የሚቀኙበት ተራ ተሰ





www.ethiopianorthodox.org

ጥቶአቸዉ ሲቀኙ የሰምና ወርቅ ቅኔአቸው መሥጢር በጣም ያስደንቅ ጀመር በዚያን ጊዜ የዋግ ሰቆጣ አውራጃ ሹም (አስተዳዳሪ) ዋግ ሹም ከበደ ስለነበሩ ክብረ በዓል በሆነ ጊዜ ሊቁ መሪጌታ ተሠራ መወደስ ቅኔ ሲቀኙ በጣም ምሥጢሩ የሚያስደንቅና የሚወደድ ስለነበር ዋግ ሹም ከበደ ይወዷቸውና ያቀርቧቸው ጀመር።

መሪጌታ ተሠራ አየለ በዚህ በቅኔ ሊቅነታቸው ብቻ ሳይሆኑ በነገሥት ትርጓሜያቸውም ተወዳጅ ሁነው ስለተገኙ ዋግ ሹም ከበደ ሠርክ ኅብስት ደርጎ ፈቅደውላቸው በአመች ሰዓት ለዋግ ሹም ከበደና ለመኳንንቱ የነገሥትን ትርጓሜ ያሰሙ ጀመር ። ከዚህ ሌላ ዋግ ሹም ከበደ ልጃቸውን ደጃች ኃይሉ ከበደንና እንደራሲያቸውን ደጃዝማች ዓለማየሁን ለሊቁ ለመሪጌታ ተሠራ አየለ ቅኔ እንዲያስምሩላቸው ስለ አዘዙአቸው በሚገባ ቅኔ አስቀኝተውላቸዋል ።

ዋግ ሹም ከበደም ደስ ስለአላቸው ሁለት ጊዜ ካባ ከነቀሚሱ ሸልማዋቸዋል ።

ሊቁ መሪጌታ ተሠራ በ1928 ዓ/ም ኢጣልያ ፋሺሽት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ለዓርበኞች ስንቅና የምሥጢር ደብዳቤ አመላላሽ በመሆን ብዙ ቁም ነገሮችን ለውድ አገራቸው አበርክተዋል ።

በላስታ አውራጃ ውስጥ ከቅዱስ ላሊበላ ደብር አጠገብ የምትገኘውን የአሽተን ማርያም ንዋያ ቅዱሳት ከታወቁት ታላቅ አባት ከአባ ደበሉ ጋር በስውር ቦታ በማስቀመጥ ከጠላት እጅ አድነዋል ። አባ ደበሉም በፋሽሽት እጅ ሲገደሉ መጻሕፍቶቻቸውን ስብስበው ለአሽተን ማርያም ደብር አስረክበዋል ።

ጠላት ድል ሆኖ ነፃነታችንን ባገኘን ጊዜ የመሪጌታ ተሠራ ታላቅ ቁም ነገራቸው በመንግሥት በቤተ ክህነት ታውቆ ስለነበር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከቀድሞው ንጉሥና ከአቡነ ባስልዩስ ዘንድ ካባ ክብር የተሠራ መቋሚያና ጸናጽል ተሸልመዋል።



እንዲሁም በላስታ አውራጃ ከታወቀው ታላቅ ደብር በቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ቤተ ክርስቲያን በቅኔ መምህርነት ተመድበው ቤተክርስቲያኑን በማገልገልና ቅኔም በማስተማር ብዙ ደቀመዛሙርት አፍረተው ለቅድት ቤተ ክርስቲያናችን አብርክተዋል ።

ከብዙ ተማሮቻቸውም መካከል የቅኔ መምህር ሁነው ዛሬ በማስተማር የሚገኙት ፡

፩) የደብረ ዘመዶው መሪጌታ ሀብቴ

፪ኛ) የዋሮ ሚካኤል መሪጌታ ቾኮለ

፫ኛ) የመርጦ ኢየሱስ መሪጌታ

፬ኛ) የቡግና ዓይና ኢየሱስ መሪጌታ ከንፉ

፭ኛ) የይሞርሃው መጋቢ ውቤ

፮ኛ) የወቂጣው የኔታ ደስታ ወዘተ ናቸው ።

መሪጌታ ተሠራ አየለ በሕግ ሚስት አግብተው ስማቸውን የሚያስጠሩ አንድ ወንድንና ሁለት ሴቶች ልጆችን ወልደዋል።

ሊቁ መሪጌታ ተሠራ ከቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ወደ ቅዱስ ላሊበላ ደብር በመዛወር ብዙ ዘመን ቤተ ክርስቲያኑን አገልግለዋል ወደ መንግሥትም እየተላኩ ብዙ ቁም ነገሮችን ፈጽመዋል ።

ከቅዱስ ላሊበላ ሁለት መምህራንም ካባ ተሸልመዋል ። በመጨረሻም ጉልበታቸውና ዓይናቸው ደክሞ ከቤት መዋል እንደ ጀመሩ በእጃቸው የጻፏቸውን ድጓና ግሥ የነገሥት ትርጓሜ ምልክት ለአሽተን ማርያም ደብር አውርሰዋል ከባና ቀሚሶቻቸውንም ፤ ለደረዋ ማርያም ለቤተ አንበሳ ማርያም ፤ ለግብፃዊ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያኖች በስጦታ መልክ አበርክተዋል ።

ከዚህም በኋላ መንኩሰው ዕድሜን ጠግበው የልጅ ልጅ አይተው በጾምና በጸሎት እንደተወሰኑ በተወለዱ በ፹፫ ዓመታቸው በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነሐሴ ፲፱ ቀን በቅዱስ ላሊበላ ደብር አርፈው አስከሬናቸው በቁመናቸው ባሠሩት መቃብር ቤት አርፏል ።

ሞት ለሰው ልጅ ሁሉ የማይቀር ዕዳ ስለሆነ ነው እንጂ በእኒህ ታላቅ ሊቅ ሞተ ያላዘነ የለም ። አሁንም እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ከማኅበረ ጻድቃን ነፍስ ጋር ይደምራት ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ትጸልያለች ።

የታሪኩ አቅራቢ ገብረ መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም



ተዘግቶ ጉዞአቸውን በመቀጠል አዳር ዋጃ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ በ፮/፪/፲፱፻፹፬ ዓ.ም ሐዋርያዊ ጉዞአቸውን ፈጽመው በሰላም ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ወልድያ ወደ ሚገኘው መንበረ ጵጵስናቸው በሰላም ገብተዋል ብፁዕነታቸውም ከ፳፭/፩/፲፱፻፹፬ —፮/፪/፲፱፻፹፬ ዓ.ም በአደረጉት ሐዋርያዊ ጉዞ ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናትና መምህራንና አቅመ ደካማዎች ብር ፰፻፹፬ ከግል ገንዘባቸው ወጭ በማድረግ እረድተዋል።

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ መዓዛ አስማማው

ጥበባቸው ከዓለም አድናቆትን ያተረፉትን የዕቴጌ ጣይቱ ብጡል

## ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል ምን ሠርተው እንዳለፉ ያውቃሉ?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መንፈሳዊ ሴቶች በምንመለከትበት ጊዜ የያዝነው መጽሐፍ ቅዱስ ምዕት ዓመታት በፊት ተጽፎ ያበቃ ቢሆንም ሳያቋርጡ ለሚተኩ መንፈሳዊ ሴቶች ምስክርነት ተጨባጭ መልሶችን ለመስጠትና የመልሶች መዝገብና ምንጭ ከመሆን አላቋረጡም ።

ዮዲት መጽሐፈ ዮዲት አስቴር መጽሐፈ አስቴርም ሌሎችም ከዚህ ቀደም በዓምዳችን የጻፍናቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በጾም በጸሎት በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የሀገራቸውንና የወገናቸውን ጠላት ድል እንዳደረጉ እንረዳለን በዚህም አንጻር በየዘመኑ የተነሱ ሴቶች በመንፈሳዊ ሕይወት ፣ በጥበብ በዘዴ ተጠቅመው ጠላቶቻቸውን ድል የሚያደርጉ የሀገራቸውን ክብር የሚያስጠብቁ በቀላሉ የሚታዩ አልሆኑም።

በሀገራችን በመንፈሳዊ ትምህርት ብስለታቸው ፣ በጾም በጸሎት ጽሙድነታቸው ታዋቂ በጥበብና በዘዴአቸው ተደናቂ የሆኑት ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል ለሀገሬ ለወገኔ ማለትን ያስቀድሙ እንደነበረ ታሪክ ከሥራቸው ማኅደር ጋር ምስክርነቱን ይሰጣል ።

በመንፈሳዊ አገልግሎትና ትምህርት በሀገር ግንባታና በፖለቲካ ጥበባቸው ከዓለም አድናቆትን ሙሉ ሥራቸውን ለመዘርዘር ዓምዳችን በቂ ባይሆንም በመጠኑ ለማሳየት እንሞክራለን ።

<u>በመንፈሳዊ ትምህርትና አገልግሎት</u>

ከማንኛውም ሥጋዊ ነገር ሁሉ ለመንፈሳዊ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍቅርና አስተያየት የነበራቸው ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል ። መንፈሳዊ ት/ቤቶችን ከማቋቋማቸውም በላይ ብዙ ሊቃውንት ተምረው ለቤተ ክርስቲያን ብቁ ሆነው እንዲገኙ አድርገዋል ።

በቤተ ክርስቲያናችን የጾም ሥርዓት ጊዜም በጾመ ኢየሱስ በፍልሰታ በጾመ ማርያም እንደ አንድ ተራ ምእመን መስለው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ያዳምጡና በሚፈለጉ ነጥቦች ላይም ከሊቃውንቱ ጋር ይወያዩ ነበር ። ሊቃውንቱንም እያስጠሩ ይሾሙና ይሸልሙ ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜም እንዲስፋፋና ጉባዔውም እንዲበረታታ እጅግ ይጥሩ እንደነበረ የታሪካቸው ሂደት በጉልህ ያስረዳል ።

<u>በሀገር ግንባታ በኩል</u>

በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተችው የአ.አ ከተማ መቆርቆር በዕቴጌ ጣይቱ ብጡል ከተጠናቀቁት የግንባታ ሥራዎች ዋናው ነው ። ቤተ መንግሥቱ እንጦጦ በነበረ ጊዜ ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል ከምኒልክ ጋር የዛሬውን ፍልውሃ አካባቢ እረፍት ለመውሰድ ያዘወትሩት እንደ ነበር ከታሪክ አዋቂዎች ይነገራል ። የፍልውሃን አካባቢ በሚጎበኙበት ጊዜ ከድንኳናቸው ደጃፍ ሆነው ሙቀቱንና የሀገሪቷን ውበት ተመለከቱ ። ከዚህች ሥፍራ ቦታ ይሰጠኝና ቤት ልሥራ በማለት ዳግማዊ ሚኒልክን ጠየቁ ። ንጉሡም ስለፈቀዱላቸው ጊዜያዊ ማረፊያ ቤት አሠሩ። ሥፍራው ጫካ ስለነበር እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ የፈካ ጥሩ አበባ አገኙ አበባውንም ቀጥፈው እያገላበጡ ካዩ በኋላ ይሄ ከተማ አ.አ. መባል አለበት ብለው እንደ ሰየሙ ከታሪካቸው መረዳት ይቻላል ።

<u>በፖለቲካ ተግባሮች</u>

ጣይቱ ብጡል በፖለቲካ አስተዳደር የነበራቸው ችሎታና ተግባራዊ እንቅስቃሴ በታሪክ አዋቂዎች ዘንድ ተደናቂነትን አትርፎላቸዋል ። በየጊዜው ይነሱ በነበሩ የሀገር ጉዳዮች ላይ ይይዙት የነበረው አቋም ይሰጡት የነበረው ውሳኔና ያስተላልፉት የነበረው ትእዛዝ ፣ ተሰሚነትና ተቀባይነት እያገኘ እንደመሄዱ መጠን ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ይሄድ ለነበረው የፖለቲካ ሥልጣናቸው ዓይነተኛ ምክንያት ነበር ።

ኅዳር ፬ ቀን ፲፰፻፸፱ አፄ ምኒልክ በአርሲ በኩል ወደሐረር በዘመቱበት ጊዜ ደጃች ወልደ ገብርኤል ጨርጨርና ኢቱን ተሹመው



www.ethiopianorthodox.org

ሳለ ለሐረር ዘመቻ የበኩላቸውን ዝግጅት በማጠናቀቅ ላይ እንዳሉ ወታደሩ እየከዳቸው ተቸገሩ ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል በሰሙ ጊዜም የሚከተለውን ዘዴ ተጠቅመው ወታደሮቹን እንዳሰሰሯቸው ጸሐፈ ትእዛዝ ገ/ሥላሴ ስለዳግማዊ ምኒልክ በጻፉት መጽሐፋቸው ገጽ ፩፻፵፱-፫ እንዲህ ሲሉ ጠቅሰውታል ።

ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል እንኩበርም ይፍረታም ግሼንም መርሐቤቴም ላለው ምስለኔ ሁሉ ደብዳቤ ላኩ ። ቃሉም ይህ ነው ከደጃች ወልደ ገብርኤል (ጋር) ዘንድ የመጣውን ሰው ቀለብ አደረጀ ብዬ ወደእናንተ እሰዳቸዋለሁ እኔ ከዚያ ያለውን ማክሰኞ ቀን እሥራዋለሁ ። እናንተም በዚያ ቀን መሣሪያውን እየተቀበላችሁ ግንድ እየፈለፈላችሁ እሠሩ አሉ። በግንዱም እሠሩ ማለትዎ (ማለታቸው) ባላገሩ ሁሉ እግር ብረት አያገኝም ስለማለት ነው ። ለራስ ጎበናም የከዱትን መኳንንቶች ወደእናንተ እሰዳለሁና ከደህና ሥፍራ እሠሯቸው ብለው ላኩ ።

ወታደሩም ደብዳቤውን ተቀብሎ እንደ ፆርዮ ጠግረ ሞቱን እየያዘ ሄዶ ከአዋሽ ወንዝ እንስቶ እስከጎልማሴ ቀብር ድረስ በአንድ ዕለት ማክሰኞ ቀን ተይዞ ታሥሮ አደረ ሰው ሁሉ ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል ባደረጉት ነገር (ዘዴ) እጅግ ተደነቀ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተሳትፎአቸው የገነነውና በአገር አስተዳደርም ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ሚያዝያ ፳፭ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ/ም በውጫሌ ላይ ከኢጣሊያ ጋር ተፈርሞ በነበረው የተጭበረበረ (የተሳሳተ) ውል ነበር ። በጣልያንኛው ትርጉም ሀገሪቷን ነፃነት እንደሌላት ጥገኛ በማድረግ ከውጭ ሀገር መንግሥታት የሚኖራት ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት አማካኝነት መሆኑን ሲሰሙ ድርጊቱ አስቆጥቷቸዋል ።

ከዚህም የተነሳ የኢጣሊያ ጉዳይ አስፈጻሚ የነበረውን ኩንት አንቶሊ የፈጸመው ድርጊት የአገሪቷን ክብር የሚነካ መንግሥቱንና ሕዝቡን የሚያዋርድ በመሆኑ ገስጸውና አዋርደው ቁርጥ ውሳኔ እንዲወሰንበት አደረጉ ለአድዋ ጦርነት ቀስቃሽ ምክንያትና ዋነኛ መንስኤ የሆነው ይኸው ነበር ።

ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል በመቀሌ በተደረገው ጦርነት ታላቅ ጀብዱ ፈጽመዋል ። የመቀሌን ከተማ ይዞ የነበረው የጣሊያን ሠራዊት ሳያስበው በምሥጢር ውሃ የሚጠጣበትን ወንዝ በመሳሪያ የተጠናከሩ ወታደሮቻቸውን ልከው በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ ወታደሩ እንዳይቸገር ስንቅ እየላኩና የሞራል ድጋፍ እየሰጡ እንዲበረታታና ኃይል እንዲያገኝ በማድረጋቸው የጣሊያን ሠራዊት ከሚጭናቸው በቅሎዎችና ፈረሶች ጋር በውሃ ጥም አለቀ በመጨረሻም እርቅ ጠይቆ መቀሌን ትቶ ወደ አድዋ እንዲሄድ ተስማማ ።

በተጠቀሙት ዘዴም ከሕዝቡና ከመኳንንቱ ታላቅ ምስጋና አግኝተዋል ። የካቲት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ/ም በተደረገው ጦርነት ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል ጀግንነት የተላበሰ ጀብዱ ፈጽመዋል ሠራዊቱ ወደፊት እንዲገፋ ሴቶችን ከፊትና ከኋላ አሰልፈው "ወንዶቹ ንቁ አገራችንን ጠብቁ እንኳን ወንዶቹ እንዋጋለን ሴቶቹ" የሚል መፈክር አስይዘው ሞራል በመስጠት ሲዋጉና ሲያዋጉ ውለዋል ። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ኩታቸውንና ሻሻቸውን እየቀደዱ የቆሰለውን ሠራዊት ቁስሉን በማጠብ የተጎዳውን ቀና አድርገው ውሃ በማጠጣት ምግብ እንዲቀምስ በማድረግ ከተከታዮቻቸው ሴቶች ጋር ወገናዊ ርኅራኄ ፈጽመዋል ።

እንግዲህ የዕቴጌ ጣይቱ ብጡል መንፈሳዊ ሥራና የጀግንነት ታሪክ ከመልካም ሥራው ጋር ሲታወስ እንደእንቁ እያበራና መሰል የሴት ጀግኖች እየታደሱበት እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ይኖራል ።

# ጤናችን

## አስም

የአስም ህመም ያለበት ሰው እንደ ልቡ አየር ወደ ውስጥ የማስገባትና የማስወጣት ችግር አለበት ። ህመምተኛው ወደ ውስጥ በሚተነፍስበት ጊዜ በማዳመጫ ሲዳመጥ የማፏጨት ዓይነት ድምፅ ይሰማል ። የአስም ህመም አየር ወደ ውስጥ ሲሳብ የአንገት ሥር አካባቢ የሚገኙ ክፍሎችና በጐን የደረት አጥንቶች መካከል ያለው ቆዳ ወደ ውስጥ ይሰረጉዳል ። አንገት ሥር ያሉ የደም ሥሮች ያለመጠን በመወጣጠር ይገተራሉ ። ትኩሳት አብዛኛውን ጊዜ አይኖርም ።

አስም ብዙውን ጊዜ በሕፃንነት ወይም በወጣትነት ዕድሜ ይጀምርና እስከ ዕድሜ ልክ ድረስ እያስቸገረ ሊቆይ ይችላል ። ምንም እንኳ ተላላፊ ባይሆንም አስም ካለባቸው ወላጆች የሚወለዱ ልጆች ለዚህ ህመም ተጠቂዎች ናቸው ። የአስም ህመም ከበድ ባለሁኔታ የሚነሳው በታወቀ ወራትና በሌሊት ነው አስም ለአያሌ ዓመታት ባሰቃያቸው ሰዎች ላይ ኤምፊሱማ የተባለ የሳንባ ጤና መታወክ ሁኔታ ሊያስከትል ይችላል ።

የአስም ህመም ለአካል የማይስማማ ወይም የሚያስቆጣ ነገር ሲጤስ ወይም ሲሸተት ሊነሳ ይችላል ። ህፃናት ጉንፋን በሚይዛቸው ጊዜ አስም ሊቀሰቀስባቸው ይችላል ። በአንዳንድ ሰዎች ላይ ንዴት ሃሳብና ብስጭት አስምን የመቀስቀስ ጠባይ አለው ።

የአስም ህመም ከቤት ውስጥ በከባድ ሁኔታ የሚያሰቃይ ስለሆነ ህመምተኛው ወደ ውጪ ወጥቶ ንጹሕ አየር እንዲያገኝ መደረግ አለበት የአስም ህመምተኛውን ማፅናናትና ማበረታታት ይገባል ህመምተኛው ብዙ ፈሳሽ ነገሮችን እንዲጠጣ ከተደረገ ዘግቶ የሚያፍነውን የመዝለግለግን ወፍራም አክታ ስሚያቀጥንለት እንደልቡ ለመተንፈስ ይችላል ውሃ አፍልቶ እንፋሎቱን መታጠን ህመሙን ላመስታገስ ይጠቅማል ። መለስተኛ ለሆነ በአስም መታፈን ችግር የመተንፈሻ ቧንቧዎችን ሊከፍቱ የሚችሉ እንደ ኤፌድሪን ወይም ቴዮፊሊና የመወሳሰሉትን በመስጠት ነው ። አስሙ ከባድ ሆኖ ከፍተኛ የማፈን ችግር ሲያስከትል አድሬናሊን ለአዋቂዎች ½ አምፑል (ብልቃጥ) ልጆች ደግሞ ¼ አምፑል መስጠት ይኖርበታል ።

ህመምተኛው ትኩሳት ካለው ከ3 ቀኖች በላይ ከቆየ በተጨማሪ ቴትራ ሳይክሊን ወይም ኤሪይትሮ ማይሲን ፀረ ህዋሳት መድኃኒቶች መስጠት ነው አልፎ አልፎ እንደወስፋት ያሉ ጥገኛ ትሎች በህፃናት ላይ ለአስም ህመም መቀስቀስ ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ መኖራቸውን አረጋግጦ ፒፒራዚን መስጠት ይገባል ።

ለአስም ህመምተኛው እስፈላጊው ሁሉ ተደርጎ ካልተሻላቸው የተሻለ ዕርዳታ ወደሚገኝበት የጤና ድርጅት በአስቸኳይ መላክ ይኖርበታል ።

### የመከላከያ ዘዴዎች

የአስም ህመምተኛ ህመሙን ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ጠረኖችንና ምግቦችን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለበት ። ህመምተኛው የሚተኛበት ቤትም ሆነ የሥራ ቦታ ንጹሕ መሆን ይገባዋል ። ዶሮችና ለማዳ እንስሳት ወደ መኝታ ቤት እንዳይገቡ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። የሌሊት ልብስ ብርድ ልብስ አንሶላ ፍራሽና ትራስ ፀሐይ ላይ ማስጣት ጠቃሚ መሆኑን መሞከር ተገቢ ነው ። የአስም ህመምተኞች ከተበከለ አየር ራቅ ብለው ንጹሕ አየር ወደሚገኝበት ቦታ እንዲዛወሩ ከተደረጉ ሊሻላቸው ይችላል ።

የአስም ህመምተኞች ሲጋራ ማጤስ አይኖርባቸውም ሲጋራ የበለጠ ሳንባቸውን ሊያስኮጣውና ሊጎዳቸው ይችላል ። በመሠረቱ ስለበሽታው ስም መንስኤው ምልክቱ ምርመራው ወይም ህክምናው ስለመድኃኒቱ እና ስለመከላከያው ከላይ የጠቀምኳቸው ሲሆኑ በአማኞች ዘንድ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ነው ። ይህን የላከበት ዋና ምክንያት በአማኞች ላይ የሚመጡ በሽታዎች በተለያየ ምክንያት ስለሆነ ነው ለምሳሌ በዮሐ ፱ ላይ የምናየው የጌታ ክብሩ ይገለጥ ዘንድ በመጽሐፈ ኢዮብ የምናነበው እምነትን ለመፈተን ሲሆን በአጠቃላይ በተለያየ መልኩ አማኞች ሊታመሙ ይችላሉ ለዚህ ሁሉ መድኃኒቱ ግን ራሱ እግዚአብሔር መሆኑ ግልጥ ነው ።

ሳይንስና ቴክኖሎጂ በዘመናዊ ህክምና የምንጠቀምባቸውን ነገሮች ከአፈር ፣ ከዕፀዋትና ከእንስሳት ከመሳሰሉት አዘጋጅቶ ቢያሳየንም በኦሪት ዘፍጥረት ምዕ ፩ እንደምናየው እግዚአብሔር ለሰው ልጆችና ለፍጥረታት ሁሉ መኖሪያ የምትሆነዋን ዓለም ሲፈጥር እነዚህ ሁሉ እንደተገኙ እናያለን ።

ስለዚህ ምንም መንፈሳውያን ብንሆንም እግዚአብሔር ለሥጋችን መዳኛ ይሆነን ዘንድ ጥበብን ና ማስተዋልን ሰጥቶአቸው በሳይንስ ተመራምረው ቀምመው ሐኪሞች የሚያዘጋጁልንን መድኃኒት ልንተወው ችላ ልንለው አይገባም ።

መላከ ሕይወት ይትባረክ ዓለሙ

መምህር አበበ…

(ከገጽ ፲፬ የዞረ)

ሉም ሰላምን ነው ፤ ሰላም ፈላጊው እርሳቸው ብቻ አይደሉም በሀገር የሚኖር ፍጡር ሁሉ ሰላም ፈላጊ ነው እግዚአብሔር አምላክ ያየነውን የሰላም ጨላንጭል የበለጠና የጐላ አድርጐ እንዲያሳየን ሁላችንም ወደፈጣሪያችን እንማፀናለን።

የደከሙት እንዲበረቱ የተወለዱት እንዲያድጉ የደኸዩት እንዲበለጽጉ ያልተማሩት ተምረው እንዲያውቁ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች እንዲረዱ በሀገራችን ላይ ሰላምን ያስፍንልን ። አሜ



www.ethiopianorthodox.org

# የአቶ አማረ ገዛኸኝ አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ አማረ ገዛኸኝ ከአባታቸው ከአቶ ገዛኸኝ ድንቁና ከእናታቸው ከወ/ሮ አበበች አየለ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በጋሞ ጐፋ ክፍለ ሀገር በጋርዱላ አውራጃ ልዩ ስሙ ወረዚ በሚባለው ፍራ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት [illegible] ደረስ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጊዶሌ ፊታውራሪ ገበየሁ ት/ቤትና በአዲስ አበባ ሽመልስ ሀብቴ ፪ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቀቁ ። ከዚያም ከ፲፱፻፳፬ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው በንግድ ሥራ ዘርፍ ተሰማርተው እራሳቸውን



ወንድም እህቶቻቸውን ዘመዶቻቸውንም ጭምር በማስተማርና በመርዳት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የኖሩ ፤ ሰው አክባሪ ፣ ትሁትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው ነበሩ ።

ባላቸውም መፍንሳዊ አመላከ[illegible] ዘንባሉ ከ[illegible] ተግባራቸው ይልቅ በመንፈሳዊ ሥራ አገልግሎት በማመዛዘን ከተቀደሱ ሥፍራዎች የማይለዩ በጸሎት አምላክን የሚመጠኑ የቤተ ክርስቲያን የቅርብ አገልጋይ በመሆን ፦

ሀ) የአሰቦት ደብረ ወገግ ቅድስት ሥላሴና የአቡነ ሳሙኤል ገዳም የቤተ ክርስቲያን እድሳትና የመንገድ ሥራ ማኅበር ።

ለ) የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፡፡

ሐ) በኢትዮጵያ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት

መ) በዝዋይ ደሴት የጽዮን ማርያም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ማኅበር ፤

አባልነት በገንዘባቸው ፣ በንብረታቸው ፣ በጉልበታቸውና በዕውቀታቸው ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ መሰል ጓደኞቻቸውን በማስተባበር በየአድባራቱና በየገዳማቱ በተለይም በእንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ለሚዘጋጀው በዓል ደግሰው በመጋበዝ አገልግለዋል ።

ለሰሜን ተራራ ደብረሲና እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ግንባታ የሚሆን ገንዘብ ከመርዳታቸውም በላይ ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳት ከውጭ አገር ድረስ በመምጣት አበርክተዋል ። በተጨማሪም በውጭ አገር የሚገኙት ገዳማትን በመጐብኘት በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ገዳም በልዩ ጌጥ የተሠራ መስቀል ለግሰዋል ። ምንም መልካም ሥራ ሲሠሩ ሞት የማይቀር ዕዳ ስለሆነ አቶ አማረ ገዛኸኝ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. በደረሰባቸው ድንገተኛ የመኪና አደጋ በየካቲት 12 ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቆይተው መስከረም ፲፩ ቀን በተወለዱ በ፵፯ ዓመታቸው ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸውና ከዘመድ ወዳጅ መካከል ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳቸውን በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብ ቃል ኪዳን በምትወርስ መንግሥተ ሰማያት ያሳርፋት ዘንድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ትጸልያለች ።

የዜናው አቅራቢ ዕፀ ገነት

## የግሸን…

(ከገጽ ፲፫ የዞረ)

ብር ነው ።

በተጨማሪም በመድረኩ ላይ በተሰጠው ትምህርትና በተቀነባበረው ዝግጅት ነው ፤ ይህም ገቢ ለቦታው ሁነው አገልግሎት ለሚሰጡ ታሪክን ለሚጠብቁ ከቦታው ፎሬ ሁነው በየሥራ ዘርፉ ተመድበው አገልግሎት ለሚሰጡ ሲሆን በሌላው መልኩ ደግሞ ለንዋየ ቅድሳት ለቤተ ክርስቲያን ማደሻና መጠገኛ የሚውል ስለሆነ የሁላችንም ኀብረት ነው ። የታሪክ ቦታዎችንም መጠበቅና ማስጠበቅ ማወቅና ማሳወቅ የመላው ክርስቲያን ድርሻ ነው በዚህ ዓመት ወደግሸን ማርያም በመምጣት መባ ያቀረባችሁትን የጸለያችሁትንና የተመጸናችሁትን በእግዚአብሔር ስም እያመሰገን ለሚቀጥለውም ዓመት እናተና እናንተን የመሰሉ ሁሉ መጥተው መባ ለማቅረብና ለመጸለይ እንዲበቁ መልካም ምኞታችን እንገልጻለን።



# ሰበካ ጉባኤና ርምጃው የመካነ ሥላሴ መሠረተ ልማት ሲዳሞ ሀ/ስብከት

የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በሲዳሞ ክ/ሀገር በአዋሳ ከተማ ነው በዚህ ከተማ ውስጥ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ሲገኙ ከሦስቱም አንዱ ይህ ቤ/ክርስቲያን ነው የአዋሳ መካነ ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን የተተከለው በ፲፱፻፲፮ ዓ.ም ሲሆን ባሁኑ ጊዜ በርከት ያሉ የልማት ተግባራት ተዘርግተውበት እንደሚገኝ የደብሩ ሰበካ ጽ/ቤት ያቀረበው ዘገባ በሀገረ ስብከቱ ሸኝ ደብዳቤ የተላለፈልን ያረጋግጣል ።

ዘገባው እንደሚያመለክተው ከ፲፱፻፸፭ ዓ.ም ጀምሮ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢም ሆነ ውጭ የተተከሉትና ባሁኑ ጊዜ አድገውና ለምልመው የሚታዩት አትክልቶች

፩) የባሕር ዛፍ ተክል ከ፳፭ሺህ (ሃያ አምስት ሺህ) የማያንሱ ፤

፪) ፲፭ሺህ (አሥራ አምስት ሺህ) የሚሆኑ ልዩ ልዩ ተክሎች ፤

፫) ከ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፹ ዓ.ም የበቆሎና የጤፍ አዝመራ ከ፯ እስ ፰ ኩንታል ሲመረት መቆየቱን ፤

፬) ከመስከረም ፩ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም ጀምሮ ግን በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ በርተሎሚዎስ አመራር ስጭነት በመምህር ታ ሥላሴ ይግዛው የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በመ ምሕረት ጳውሎስ ቀጸላ አበረታችነትና ድጋፍ ሰጭነት ኮሚቴው ዕቅድና ፕላን በማዘጋጀት የልማት ሥራውን ከልዩ ልዩ የዘርና አትክልት ፍሬዎች ጋር ሲያመቻች መቆየቱን ከደብሩ የተላለፈው ዘገባ በሰፊው ያብራራል ።

ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም በቁመት ፩፻፶፱ በጐን ፩፻፲ ሜትር የሆነው የልማት ቦታ ከደብሩ ሰ/ጉባኤ እስከ ፪ሺህ (ሁለት ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ወጭ ሆኖ በጥሩ ሁኔታ መታጠሩን አመልክቶ ለዚሁ ማልሚያ ፳፭ የውኃ ቧንቧ ፩፻፶ ሜትር በሚሆን ቦታ ላይ እስከ ልማቱ ቦታ መግቢያ በር ተዘርግቶ አገልግሎት መስጠቱን የልማት ኮሚቴው ያስተላለፈው ዘገባ አመልክቶ የውኃው ማስራጫ ከ፪፻ ሜትር ያላነሰ ጐማ ተገዝቶ በቦታው ካለው የጉድጓድ ውኃ አገናኝቶ በመጠቀሚያው ቧንቧና ከነሥራው ብር ፩ሺህ፩፻፲፭ ከ፶፫ (አንድ ሺህ አንድ መቶ አሥራ አምስት ብር ከሃምሳ ሦስት ሳንቲም) መክፈሉን በማብራራት አስረድቶአል ።

ከዚህም ሌላ ደብሩ ለልማቱ መገልገያ የሚሆኑ መሣሪያዎች

ሀ) አካፋ ፴፱

ለ) ጌሶ ዶማ ፳፬

ሐ) ዶማ ሹልና ባለምሣር ፫፻፶፬

መ) መቆፈሪያ ባለሦስት ጣት ፴፬

ሠ) ሬክ መጨበጫ ባለ ፲፪ ጣት ፪ ብር

ድምር ብር ፲ሺህ፺፭ (አሥር ሺህ ዘጠና አምስት ብር) ከመካነ ኢየሱስ ቤ/ክርስቲያን ለልማቱ ሥራ ድጋፍ በመስጠት በርዳታ መልክ ማግኘቱን አመልክቶ ለመጋዝና ለመዶሻ መግዣ ብር ፹፭ ለአትክልቱ የውኃ ማጠጫ ፳፪ ሜትር ላስቲክ ብር ፺፱ (ዘጠና ዘጠኝ) ገዝቶ በመጠቀም ላይ ሲሆን የልማት መሬትም ከስድስት አንድ እጅ የሚሆነው በበሬዎችና በሰዎች ጉልበት ታርሶ በብር ፲ሺህ፹ (አሥር ሺህ ሰማንያ) የተገዛው የድንች ዘር ተተክሎ ፰ ኩንታል በማምረት ለሽያጭ ማቅረቡን አክሎ ገልጾአል ።

በተጨማሪም የደብሩ ሰ/ጉ ጽ ቤት ሲያብራራ ከክፍለ ሀገሩ ግብርና ልማት ቅርንጫፍ ፩፻ ብር ገዝቶ ከልማቱ መሬት ከስድስት አራተኛ እጅ በአራት ጥማድ በሬዎች አሳርሶአል ይህ በልማት ኮሚቴው አባላትና በቤተ ክርስቲያን ካህናት ትብብር የተዘራው የበቆሎ አዝመራ የዝናም እጥረት ቢያስደነግጠውም ቀደም ብሎ ስለተዘራና እንክብካቤም ስላልተለየው ከአካባቢው ሕዝብ አዝመራ የበለጠ ውጤት አሳይቶአል። በበቆሎው ውስጥ ለዓይነት የተበተነው ቦሎቄም ከአንድ ኩንታል ያላነሰ ገቢ አስገኝቶአል ብሎአል ። የልማት ኮሚቴው አያይዞ እንደገለጸው ቦታው የሚበልጠውን የጤፍ አዝመራ የያዘ ከልማቱ መሬት ከስድስት አንድ በሚሆነው መሬት ላይ ግን የበርበሬ ምርት ታፍሶበታል ብሎአል ። ስለቀዋሚ አትክልት ሲተነትንም በልማቱ ቦታ ቀዋሚ አትክልቶች በብዛት የተከለ ሲሆን ከነዚህም



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ የብርቱካን የዘይቱን የአቡካዶ የኮክ የፓፓዬ የሙዝ የእንሰት የካርሚር ችግኞች ጸድቀው ባሁኑ ጊዜ መልካም ውጤት በማሳየት ላይ ናቸው ሲል አትቶአል ።

ይህ የለማው ቦታ ከቤ/ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ የሚገኝ ሲሆን ከቤ/ክርስቲያኑ በስተሰሜን የሚገኘው ቁመቱ ፩፻ ጎኑ ፶፪ ሜትር በሆነው ቦታ ላይ በሦስት ጥማድ በሬና በቤተ ክርስቲያኑ ካህናት ሠራተኞች በልማት ኮሚቴ አባላት የስኳር ድንች ተተክሎ መሬቱን በአረንጓዴ መልክ አሸብርቆ ነበር ። የምርቱ ውጤትም ከብር ፩፻ (አንድ መቶ ብር) ያላነሰ ተገኝቶበታል ብሎአል ።

የልማት ኮሚቴው በዚህ ሥራ ብቻ ሳይወሰን ለምርት ውጤት ማስተመጫና መሸጫ የሚሆን ከብር ፮ሺህ፭፻ (ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ያላነሰ ያስወጣል ተብሎ በተገመተው ሁለት ክፍል ቤት ተሠርቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑን አክሎ በማብራራት አመልክቶአል ።

ሪፖርቱን በማያያዝም የዚሁ ደብር መንፈሳዊ አገልግሎት ሰጪዎች ቀሳውስት ሰባት ዲያቆናት ስድስት መሪጌቶች ሁለት አወዳሾች ሁለት ያለ ደመወዝ የሚያገለግሉ አራት ልዩ ልዩ በደመወዝ የሚያገለግሉ ሰባት ከሁለት መሪጌቶች አንደኛው የንባብ መምህር ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ የቅዳሴ የሰዓታት የዜማና የአቋቋም ናቸው በዚህም መሠረት የንባብ ተማሪዎች ፶፩ የአቋቋምና የዜማ ተማሪዎች አሥር የቅዳሴ ትምህርት ተከታታዮች አሥራ ሦስት ናቸው ካህናቱና ቀሳውስቱ እንዲሁም ዲያቆናቱ የቅዳሴ የዜማ የአቋቋም የመዝሙር ትምህርት ማታ ማታ እየተጸለ መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን ያከናውናሉ ከለ በኋላ ቅዳሜና እሁድ በየሳምንቱ ከሰዓት በኋላ ለሰንበት ተማሪዎች በተለያዩ መምህራን በቂ ትምህርት በመስጠት ላይ መሆኑንና ሰበካ ጉባኤው ስለዚሁ ዐቢይ ጉዳይ ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሰጠው በሰፊው አትቶ ገልጾአል ።

ቀጥሎም ሪፖርቱን በማራዘም ሲያትት በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ የአንደኛ ደረጃ መሠረተ ትምህርት በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ጥቅምት ወር መቋቋሙን አውስቶ የትምህርት ቤቱም ደረጃ እስከ ፬ኛ ክፍል መድረሱንና ከላይ ከተጠቀሰው ዓ.ም ጀምሮ ለብዙ ወገኖች የትምህርት ጥማታቸውን በማርካት ለከፍተኛ ደረጃ ማድረሱንም አረጋግጦአል በት/ቤቱ አራት ወንዶች አራት ሴቶች በድምሩ ስምንት መምህራን እንዳሉትና የወንዶች ተማሪዎች ብዛት አራት መቶ ሰባ አምስት የሴቶች ተማሪዎች ብዛት ሦስት መቶ ሰባ አንድ በድምሩ ስምንት መቶ አርባ ስድስት እንደሚሆኑም ያስረዳል ።

መለስተኛ የጎጆ ኢንዱስትሪን በተመለከተም ደብሩ ከተተከለ ቅርብ ጊዜ ቢሆንም በመተዳደሪያው በኩል አሳሳቢ መሆኑን ጠቅሶ ራሱን ለማስቻል ልዩ ልዩ የልማት ተቋሞችን ለመዘርጋት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑንም ከገለጸ በኋላ የቤ/ክርስቲያኑ አገልግሎት እንዳይቋረጥ በማሰብ በቤ/ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ውስጥ ት/ቤት ተመሥርቶ ትምህርቱም ለቀሳውስቱና ለዲያቆናቱ እንዲሁም በመሪጌታው እንዲሰጥ የተደረገበት ምክንያት መንፈሳዊ አገልግሎት ሰጭ ካህናትን በቅርብ ለማግኘት ታስቦ ነው ብሎአል በማያያዝም በ፲፱፻፸፭ ዓ.ም የመጀመሪያው ሰበካ ጉባኤ ስብሰባ አዲስ አበባ በፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት በተመራበት ወቅት ደብሩ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ራሱን ለማስቻል የእህል ወፍጮ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መመሪያ ጠይቀን ተስፋ በማግኘታችን በደስታ ብንጠብቅም የተሰጠንን ተስፋ እስካሁን አለማግኘታችን ያሰብነው የልማት እንቅስቃሴ ግቡን ሊመታልን አልቻለም ሲል ገልጾአል ።

ስለዚህ ዐቢይ ጉዳይ አያይዞ ሲያስረዳም ወፍጮውን የአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ በናፍቆት እየጠበቀነው ምክንያቱም በአጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ ስም የሚፈጭ እህል በረከቱና ረድኤቱ እጅግ የላቀ በመሆኑ ነው እንደአጋጣሚ ሆኖ የአዋሳ ከተማ የወፍጮ እንዱስትሪ በጠቅላላ በቤተ ክርስቲያናችን በስተምሥራቅ በኩል ከልማት ቦታዎች ጀምሮ እንዲቋቋም ከከተማ ልማት መፈቀዱንና ከአሥራ አምስት ያላነሱ ግለሰቦችም ቦታ ተረክበው ወፍጮውን ሊያቋቁሙ በመዘጋጀት ላይ ስለሆኑ ቦታው ጨርሶ ከመያዙና ለቤተ ክርስቲያኑ የሚገባውንም ቦታ ከመወሰዱ በፊት ልማት መመሪያው የሰጠውን ተስፋ ችግራችንን አይቶ ቢፈቅድልን ደስታችን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል ሲል የደብሩ ልማት ኮሚቴ አክሎ አመልክቶአል ።



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢሮርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ.ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org